«የአዳም ፈጣሪ እኔ ነኝ ለእረፍት ሰንበትን ሠራ። አይሁድም በማን ሥልጣን ይህን ታደርጋለህ አሉት፤ እርሱም እኔ እሠራለሁ እናንተም ሥራዬን እመኑ አላቸው። የሰንበት ጌታ እኔ ነኝ፤ የሰንበት ጌታዋ የአብ አንድያ ልጁ ነው።»

*ቅዱስ ያሬድ (ጾመ ድጓ)*

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፬ የሕፃናት ዓምድ

፲፱ ትዝብት

፳፩ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

<u>አዲስ አበባ</u>

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ለተገደሉ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ድጋፍ እንደምታደርግ አስታወቀች

## .ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል በግፍ ለተገደሉ ኦርቶዶክሳውያን ኀዘናቸውን ገልጸዋል



*ብፁዕ አቡነ ማቲያስ ከሩሲያው ፓትርያርክ ከብፁዕ አቡነ ኪሪል ጋር*

*በካሣሁን ለምለሙ*

የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሰሞኑን በኦሮምያ ክልል ሆሮ ጉድሮ ወለጋ ዞን አቢ ደንጎሮ ወረዳ ዴቢስ ቀበሌ በታጣቂዎች ለተገደሉ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ድጋፍ እንደምታደርግ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል ማስታወቃቸውን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ አስነበበ።

ቅዱስነታቸው ይህንን ያስታወቁት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማት በጻፉት የአጋርነትና የድጋፍ ደብዳቤ እንደሆነ ዘገባው አስረድቷል።

በንጹሓን ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው ጥቃት የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እንዳሳዘነ የገለጹት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል ለሟቾች እንጸልያለን ብለዋል። በሃይማኖታቸው ብቻ ግፍና በደል ለሚደርስባቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ጠንካራ ድጋፍ እንደሚያደርጉ መግለጻቸውን ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል።

ሰሞኑን በኦሮምያ ክልል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ላይ በተፈጸመ አሰቃቂ ጥቃት በርካታ ምእመናን፣ እናቶች፣ ሕፃናትና ካህናት መገደላቸውን ቅዱስነታቸው በላኩት ደብዳቤ አስታውሰው ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስና ለተጎጂ ቤተሰቦችም መጽናናትን ተመኝተዋል።

በንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸመ ያለው አሰቃቂ ጥቃት የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እጅግ ያሳሰበ ጉዳይ መሆኑን የገለጡት ቅዱሰነታቸው ቤተ ክርስቲያናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያኖች በሀገራቸው በነፃነትና በደኅንነት እንዲኖሩ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንደምታደርግ "ቃል እገባለሁ" ሲሉ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አሳውቀዋል።

"በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በእምነታቸው ምክንያት የሚገደሉ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ፍትሕ እንደሚያገኙ ተስፋ አደርጋለሁ" ማለታቸውንም ከደብዳቤው መረዳት ተችሏል። የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በእምነታቸው ምክንያት በሚሰደዱ ኢትዮጵያውያንና በሌሎች ቦታዎች የሚገኙ ክርስቲያኖችን ከጥቃት ለመከላከል ቁርጠኛና ግንባር ቀደም እንደሚሆኑ ቅዱስነታቸው የገልጠዋል።

እ.ኤ.አ በታኅሳስ 2020 ‹‹የአፍሪካ ክርስቲያኖችን ከጥቃት መከላከል›› በሚል ስያሜ የተካሄደው የቪዲዮ ኮንፈረንስ የተዘጋጀው በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በሩሲያ የሃይማኖት ነፃነት አስጠባቂ ማኅበራት አነሳሽነት መሆኑ ተገልጿል። ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ፣ የፓን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ማኅበር የኮንፈረንሱ አጋሮች ከተሳታፊዎች መካከል እንደነበሩ ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል።

# የወላይታ ዞን አስተዳድር ሀ/ስብከቱ ላቀረባቸው ቅሬታዎች መፍትሔ ለመስጠት ኮሚቴ ማዋቀሩን ተገለጠ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በወላይታ ሀገረ ስብከት የወላይታ ዞን ፕሮቴስታንት የመንግሥት አመራሮች ቤተ ክርስቲያንን ሆን ብለው ላለፉት ዐሥር ዓመታት ሲበድሉ እንደነበር የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መልአከ ሰላም ቀሲስ ቦኪቻ ኢንጋ ገለጡ፡፡

የዞኑ ፕሮቴስታንት የመንግሥት አመራሮች በተለይ በገጠር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ይዞታ ላይ ከፍተኛ በደል ይፈጽሙ እንደነበር ያስታወቁት ሥራ አስኪያጁ ችግሩን ከመሠረቱ ለመፍታትም ከወረዳ እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ደርሶ አቅጣጫ የተቀመጠ ቢሆንም አመራሮቹ ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኞች ሳይሆኑ እንደቀሩም ተናግረዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ያሏት ጥያቄዎች በሙሉ እንዲመለሱ ላለፉት ዐሥር ዓመታት ለወላይታ ዞን አመራሮች አቤቱታ ስታቀርብ ብትቆይም በአመራሮቹ በኩል ምንም ዓይነት አወንታዊ ምላሽ እንዳልተሰጠ ሥራ አስኪያጁ አስታውሰዋል፡፡

በቅርቡም አንድ የፕሮቴስታንት ‹‹ሰባኪ ነኝ›› የሚል ግለሰብ ወላይ ሶዶ ከተማ በሚገኙ አጥቢያዎች እየዞረ በጥሩምባ በመታገዝ ‹‹የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጠንቋይ ናት፤ ከዚህ ውጡ፤ ያለበለዚያ ኢየሱስን አታገኙም›› እያለ ሲረብሽ በአግባቡ ይዘን ለሕግ አካላት ብናቀርብም ሕጋዊ ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ድርጊቱን የተቃወሙ ኦርቶዶክሳዊ ወጣቶችን አሰረዋል፣ ደብድበዋል እንዲሁም አንገላታዋቸዋል ሲሉ ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡

“የታሠሩ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶችን ከእስር ለማስፈታት ጥረት በምናደርግበት ወቅትም የአካባቢው የፀጥታ ኃይሎች በምእመንና በእኔ ላይ ተጨማሪ ወከባና ድብደባ ፈጽመዋል” ያሉት ሥራ አስኪያጁ “ከፖሊስ ጋር በተደረገው እልህ አስጨራሽ ሙግት የታሠሩ ወጣቶች ወዲያውኑ ከእስር እንዲፈቱ ስናደርግ ቤተ ክርስቲያንን ሲያንቋሽሽ የነበረው ግለሰብም በድጋሚ እንደዚህ ዓይነት ተግባር እንዳይፈጽም ፖሊስ ጣቢያ ፈርሞ እንዲወጣ የፀጥታ ኃይሎችን ጠይቀናል” ብለዋል፡፡

ሆስፒታሎችን ጨምሮ በአንዳንድ የመንግሥት ማኅበራዊ ተቋማት ላይ ፕሮቴስታንት ሠራተኞች በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ እያደረሱ ያሉትን ሃይማኖታዊ ትንኮሳ እንዲያቆሙ ለዞን አስተዳዳሪው እንዳሳወቁ ያስረዱት ሥራ አስኪያጁ ዞኑም ቤተ ክርስቲያን የምታነሳው ጥያቄ በሙሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመመለስ ቃል ገብቶ ሁከት ያስነሳው ግለሰብና ድብደባና ወከባ የፈጸሙ የፖሊስ አባላት በሕግ እንዲጠየቁ አቅጣጫ መቀመጡን ተናግረዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አያይዘውም “በዞኑ አመራሮች የተወሰኑ ውሳኔዎችንና የቤተ ክርስቲያንን ጥያቄ ሁሉ ለማስፈጸምም ዝግጁ ነን ካሉ በኋላ በግለሰቡም ሆነ ግፍ በፈጸሙ የፖሊስ አባላት ላይ ሕጋዊ የርምት ርምጃ እንዲወስድባቸው ሰሞኑን ክስ እንመሠርታለን” ብለዋል፡፡

የወላይታ ዞን አስተዳዳሪ ዶ/ር እንድርያስ ጌታ በበኩላቸው የወላይታ ሀገረ ስብከት ያቀረባቸውን ቅሬታዎች በሙሉ ተመልክተው ለእያንዳንዱ ቅሬታ መፍትሔ ለመሥጠት ኮሚቴ ተዋቅሮ እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልጠው በወላይታ ሶዶ ከተማ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ሁከትና ብጥብጥ ያስነሳው ግለሰብም ሆነ አባቶችንና ምእመናንን ያዋከቡ የፖሊስ አባላትም በሕግ እንደሚጠየቁ አስረድተዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በድለውኛል ባለቻቸው አካላት ላይ ክስ እንድትመሠርትና ድጋፍ እንደሚያደርጉ የገለጡት አስተዳዳሪው በቀጣይም በወላይታ ዞን ባሉ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ያለውን የይዞታ ጥያቄ ዞኑ ትኩረት እንደሚሰጠውና ከሀገረ ስብከቱ ጋር ተናበ እንደሚሠራ እንዲሁም ለተነሱት ቅሬታዎች ሁሉ አፋጣኝ መልስ ለመስጠት አቅጣጫ ማስቀመጡን አስገንዝበዋል፡፡

በተከለከሉ ቦታዎች በተለይም በመንገድ ላይ፣ በሌሎች እምነት ተቋማት አቅራቢያ እንዲሁም በገበያ ቦታ ላይ በአጠቃላይ ከራሳቸው ቤተ እምነት ውጭ አግባብ ባልሆነ መንገድ ‹‹ወንጌል እንሰብካለን›› በሚሉ አካላት ላይ ዞኑ አስተማሪ ርምጃ እንደሚወስድ የገለጡት አስተዳዳሪው “በሕክምና ተቋማትና በሌሎች ማኅበራዊ ተቋማት ላይ የሚፈጸመውን ሃይማኖታዊ ትንኮሳን ጭምር ለማስቀረት ርምጃ እንወስዳለን” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# የክርስትናችንን እንቅፋት ከፊታችን እናስወግድ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ልዩ ልዩ መልክ ባህልና ቋንቋ ያላቸው ሕዝቦች የሚኖሩባት ታላቅ ሀገር ስትሆን ከ፹ በላይ ቋንቋዎችም ይነገሩባታል፡፡ ከነገድ እና ከወገን የሚበዙት የሚኖሩባት ሁሉንም አቅፋ የያዘች እጀ ሰፊ ሀገር ናት፡፡ የረጅም ዘመን ታሪኳም የሚያሳየው ሕዝቦቿ ተፋቅረው እና ተከባብረው እንደ አንድ ልብ አሳቢ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው መኖራቸውን ነው፡፡ ለዚህም በተለያየ ጊዜ ሊወራት የመጣውን የጣሊያን ወራሪ ኃይል መክታ ከሀገር ያስወጣችበት ታሪክ ቋሚ ምስክር ነው፡፡ ሕዝቧ እንደዛሬ የዘር ቋጠሮ ሳይፈታ ፤ በወንዝ እና በድንበር ሳይወሰን ከአራቱም አቅጣጫ በመትመም የጣሊያንን ሠራዊት ድል አድርጎ በዓለም ላይ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከፍ ብሎ እንዲጠራ ኃይል እና ብርታት ሆኖ ነበር፡፡

የዚህ ሁሉ ማጥበቂያው ድር እና ማግ ሀገራችን ከጥንት ክርስትናን መቀበሏ እና የክርስቲያን ሀገር መሆኗ፣ ሕዝቡም ሆነ ነገሥታቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡ ቃለ ወንጌልን በተግባር ሲፈጽሙ ለመኖራቸው ሌላው ምስክር ዘጠኙን ቅዱሳን መቀበላቸው፣ ከመካ መዲና የተሰደዱ ሙስሊሞችን ማስጠጋታቸው ነው፡፡ ሀገር በሰላም እና በአንድነት ተጠብቆ እንዲኖር፤ ሕዝቦቿ በፍቅር ተጋብተው እና ተጋምደው እንዲኖሩ ያደረጋቸው ብሎም ኢትዮጵያዊነት እንዲጠነክር በማድረግ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የክርስትናው አስተምህሮ ነው፡፡

ዛሬ ከዘመን ብዛት ይህ የመከባበር እና አብሮ የመኖር ውል ጠፍቶ፣ በጠንካራ ዓለት ላይ የተመሠረተው አንድነታችን ተሸርሽሮ ዥንጉርጉርነቱና መለያየቱ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሳይቀር አጥልቶ እናያለን፡፡ በክርስቶስ ደም አንድ የሆኑ ክርስቲያኖች በዘር ተለያይተው እና ጎራ ለይተው ሲፋለሙ ማየት ቀስ በቀስ እየተለመደ መጥቷል፡፡ ከራስ አልፎ ሌሎችን የተቀበለ ክርስቲያናዊ ሰብእናችን ጠፍቷል፤ ሁሉን አንድ አደርጎ የሚያየው ዓይነችን ተንሸዋሯል፡፡ ሁሉም በየቤቱ በክርስቶስ ስለዳነው የሰው ልጅ ሳይሆን ስለጎጥ እና ስለዘር ሲያወራ ይውላል፡፡ ጾታና ዕድሜ ሳይለይ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፤ ከምእመን እስከ መነኵሴ በዘረኝነት አዙሪት ውስጥ ገብቶ ሲባዝን ይውላል፡፡ ግዴለም ወደሌሎች ማየት እና መጠቆም አያስፈልገንም ሁላችንም ከእነዚህ እንደ አንዱ ሆነናል፤ ግን እስከ መቼ?

ቤተ ክርስተያን ሄዶ የቅዱስ ወንጌልን ቃል ከመስማት ይልቅ ስለዘረኝነት መስማት የወንጌል ቃል ያህል እየተለመደ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ስም ተሰብስቦ ሀገርን ስለማይጠቅም፣ ክርስትናን ስለማያንጽ ተራ ጥላቻ እና ወሬ መስማት ከክርስትናው ተርታ የሚያስወጣ ነው፡፡ እኔ ክርስቲያን ነኝ ከሚለው ይልቅ እኔ የዚህ ዘር ነኝ፣ እከሌ የዚህ ዘር ነው ብሎ ማውራት እጅግ የሚያሳፍር ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚሸቃቅጡት . . . ›› ፪ኛ ቆሮ ፪÷፲፯ እንዳለው በቤተ ክርስቲያን አውደ ምሕረት ላይ ወንጌልን ከፖለቲካ ጋር ቀላቅሎ መስበክም ሆነ

መስማት የዘመኑ ፋሽን ሆኗል፡፡ ለዘመናት የተገነባው ማንነታችን ተሸርሽሮ ክርስትናችንን እየፈተነው ይገኛልና አጥብቀን ልንቃወመው ይገባል፡፡

ሰዎች በደልና ግፍ ሲደርስባቸው፣ ከኖሩበት፣ ሀብትና ንብረት ካፈሩበት ቀዬ ሲፈናቀሉ፣ በጅምላ ሲታረዱና ሲገደሉ እንደ ዓለማዊ ሰው ማውራት ከጀመርን ቆይተናል፡፡ በእግዚአብሔር አርአያ ስለተፈጠረው ሰው ሳይሆን የኔ ስለምንለው ዘር ስንብከነከን ፀሐይ ወጥታ ትጠልቃለች፡፡ ሆኖም ግን ማዘንና ማልቀስ ያለብን የእኔ ስለምንለው ሰው ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ሁሉ የሚገደን ልንሆን ይገባል፡፡

የሰው ልጆች ሁሉ ከአንድ አዳም ነው የመጡት ብላ በምትሰብከው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያደግን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለሰው ልጅ ማዘንን በዘር መለካት ከጀመርን ሰነባበትን፡፡ ይህን ያህል ሰው ተሰደደ ወይም ሞተ የሚለው ሳይሆን የእንትን ብሔር ተገደለ ወይም ተሰደደ የሚለውን አግዝፈን መናገር የሚቀናን እኛው ክርስቲያኖች መሆናችን ያስገምታል፡፡ በእኛ ሐሳብ የእኛ ያልሆነ ብሔር ሲሞትና ሲሰደድ ዓይናችንን የምንጨፍን ጆሯችንን የምንደፍን በተቃራኒው የኔ ለምንለው ብሔር ጎራ ለይተን በየማኅበራዊ ሚዲያው ስንሳደብና ስንራገም የምንውል እኛው ነን እኛ የቤቱ ሰዎች፡፡ ‹‹ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ›› ኤፌ ፭፥፲፮ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ዘንግተነው አለዚያም ተራ ሆኖብን ዘረኝነትን ስናሳድድ ከክርስትና እየራቅን ነውና በጊዜ ልንመለስ ይገባል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በክርስትና ጉዞዋ ውስጥ ብዙ ታሪካዊ ሰቀቃዎችን አሳልፋለች፤ ለአብነትም የዘመነ ዮዲት ጉዲት፣ የዘመነ ግራኝ . . . በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በእነዚህ ሰቀቃዎቿም የደረሰባትን መከራ በድል በማጠናቀቅ እዚህ ዘመን ላይ ደርሳለች፡፡ እኛ የዘመኑ ክርስቲያኖች ግን ከአባቶቻችን ጋር በምንም የማይገናኘውን ትንሹን ፈተና እንኳ ማለፍ አቅቶናልና ራሳችንን፣ እምነታችንን በደንብ ልንፈትሽ ይገባል፡፡ ሀገር ዛሬ ካለችበት እና ከገባችበት አዙሪት እንድትወጣ ሰላምን በመስበክ የምትታወቀው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ በክርስቶስ አንድ የሆንን ክርስቲያኖች ተግተን ልንጸልይ ልንሠራ ይገባል፡፡ ለሦስት ሺህ ዘመን ወንጌል የተሰበከልን ክርስቲያኖች እንዲሁም ለዚያን ያህል ዘመን የተገነባ የእምነትና የአብሮነት ባህልን ያዳበርን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ዛሬ ከእምነታችን እና ከአስተምህሮአችን ፈቀቅ የሚያደርግ የዘረኝነት ተራራ ከፊታችን ተገትሯል፡፡ በእምነታችን ጸንተን እንዳንኖር ፤በመንፈሳዊነትም እንዳንመላለስ የሚያደርገንን በክርስትናችን መንገድ ላይ ያለውን እንቅፋት ልናስወግደው ይገባል፡፡ በተለይም ለቤተ ክርስቲያን ቅርብ ነን ለምንል የቤቱ ሰዎች ክርስትናችንን የፈተነውን ይህን ክፉ ዘመን ተሻግረን ምእመናንንና ቤተ ክርስቲያንን ለማሻገር ከእኛ ብዙ ይጠበቃል፡፡

# መፍትሔ ያልተገኘለት የኦሮምያ ክልል ኦርቶዶክሳውያን ሰቆቃ

*በካሣሁን ለምለሙ*

ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር በመፋለምና የሕይወት መሥዋትነትን በመክፈል በመሠረቷትና ሀገር አድርገው በቆሟት ሀገራቸው ውስጥ ባይተዋር ሆነው ከመቆየታቸው ባሻገር ሠርተው ለፍተው በሚኖሩባቸው አንዳንድ ሀገራችን አካባቢዎች በአክራሪ ሃይማኖተኞችና በስሑት ትርክት አቀንቃኞች አማካኝነት እየታደኑ መገደል ከጀመሩ ግማሽ ክፍለ ዘመንን አስቆጥረዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በመሆናቸው ብቻ ያለምንም ምክንያት በአሰቃቂ ሁኔታ ይገደላሉ፤ ሀብት ንብረታቸን ይዘረፋል፤ ሆን ተብሎም ከማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ይገለላሉ፤ እንዲሁም ከአካባቢያቸው ተፈናቅለው ለሥደትና ለርኀብ ይዳረጋሉ፡፡ በአክራሪ ሃይማኖተኞችና በስሑት ትርክት አቀንቃኞች አማካይነት የሚደርስባቸው ጥቃት መነሻው ደግሞ ከዚህ ቀደም በሀገራችን የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን ‹‹በጠላትነትና በጨቋኝነት›› ፈርጆ መነሣቱ ነው፡፡ ይህ የፖለቲካ ኃይል ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን የትግል ማእከል አድርጎ ሲያጎሳቁላት፣ ሲከፋፍላት፣ ደግማና ቀኖናዋንም በመጣስ ሊያጠፋት እልህ አስጨራሽ ትግል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በመላ ሀገራችን ያሉ የዚህ ፖለቲካ ድርጅት የግብር ልጆች አሁንም ድረስ ቤተ ክርስቲያንን መድፈራቸውን ምእመናንን ማሳደድና መግደላቸውን አላቆሙም፡፡ ‹‹የፖለቲካ ለውጥ›› መጥቷል ከተባለበት ጊዜ አንሥቶም በተለይ በኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ የሚገኙ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በየጊዜው በአሰቃቂ ሁኔታ ይገደላሉ፡፡ ኦርቶዶክሳውያኑ አብዛኛውን ጊዜ በአክራሪ እስላሞች አማካይነት ይገደሉ እንጂ ከጀርባ ሆነው ጥቃቱን የሚደግፉና የሚያስተባብሩ የክልሉ የፖለቲካ አመራሮች እንዳሉ በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ ምንጮች ለመረዳት ችለናል፡፡ እነዚህ የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት ከዚህ በፊት በሥልጣን ላይ የነበረው ፀረ ኦርቶዶክስ የፖለቲካ ድርጅት ያወረሳቸውን ኦርቶዶክስ ጠልነት ሐሳብ በተግባር ሲፈጽሙ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም ላለፉት ሦስት ዓመታት ብቻ በባሌ፣ በአርሲ፣ በምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ እንዲሁም በሌሎች የኦሮምያ ክልል አካባቢዎች በርካታ ኦርቶዶክሳውያን ያለ ጥፋታቸው በአሰቃቂ ሁኔታ ታርደው ተገድለዋል፣ ከአካባቢያቸው ተፈናቅለዋል፤ ለረኀብና ለእርዛትም ተዳርገዋል፡፡

ሰሞኑንም በዚሁ ክልል በሆሮ ጉድሮ ወለጋ ዞን አቢ ደንጎሮ ወረዳ ዴቢስ ቀበሌ ላይ ይንቀሳቀስ የነበረ “ታጣቂ ኃይል” በፈጸመው ድንገተኛ ጥቃት በርካታ ኦርቶዶክሳውን ክርስቲያኖች በአሰቃቂ ሁኔታ በጥይት ተደብድበው፣ በስለትም ታርደው ተገድለዋል፡፡ ከአካባቢው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ጥቃቱን በንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ላይ የፈጸመው ‹‹ኦነግ ሸኔ›› የተባለው በአካባቢው የሚንቀሳቀስ ታጣቂ ቡድን ነው፡፡ ይህ “ታጣቂ ቡድን” በቤተ መቅደስ ውስጥ በጸሎት ላይ የነበሩ ካህናትና ምእመናንን ጨምሮ በየቤታቸው የነበሩ ንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖችን ጭምር በስለት አርዶ በመሣሪያ ደብድቦ እንደገደላቸው ታውቋል፡፡

የሆሮ ጉድሮ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ መልአከ ጽዮን ቀሲስ ተፈራ ቢሻው ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በስልክ በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት ‹‹በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው ‹‹ኦነግ ሸኔ›› የተባለው ታጣቂ ቡድን በፈጸመው ሃይማኖት ተኮር ጥቃት ቢያንስ ሃያ ዘጠኝ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ተገድለዋል›› ብለዋል፡፡ ካህናትና መምህራንን ጨምሮ እየተመረጡ የተገደሉት በሙሉ ኦርቶዶክሳውያን ብቻ መሆናቸውን የጠቆሙት ሥራ አስኪያጁ “ከዚህ በፊት በአካባቢው የፀጥታ ሥጋት

እንዳለብን ለወረዳውና ለዞን አመራሮች አሳውቀናል” ሲሉም ተናግረዋል። ‹‹በአካባቢው ያሉት የመንግሥት ባለሥልጣናት ‹‹አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ›› ዓይነት በመሆናቸው ለታጠቁ ኃይሎች ድጋፍ ከማድረግና ስንቅና ትጥቅ ከማቅረብ ውጭ የንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖችን ደኅንነት ለመጠበቅ ያደረጉት ጥረት የለም” ሲሉም አክለዋል።

በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው የተወሰነ የፀጥታ ኃይል ገብቶ የማረጋጋት ሥራ እየሠራ እንደሆነ የተናገሩት ሥራ አስኪያጁ ‹‹ጥቃት ያደረሰው ‹‹ኦነግ ሸኔ›› የተባለው ታጣቂ ቡድን ጥቃት ካደረሰበት አካባቢ ላይ በቅርብ ርቀት በሚገኝ ጫካ ውስጥ መሽጎ ይገኛል›› ብለዋል። በተለያዩ አካባቢዎች የመሸገው ይህ ታጣቂ ቡድን በአካባቢው ዘላቂ ሰላም እንዳይኖርና ሕዝበ ክርስቲያኑ ሥጋት ላይ እንዲወድቅ አድርጎታል፤ በቋሚነት ታጣቂ ኃይሉን ከአካባቢው ማጽዳት እስካልተቻለ ድረስ ዘላቂ ሰላምን ማምጣት እንደማይቻል አክለው አስረድተዋል።

በሆሮ ጉድሮ ወለጋ ሀገረ ስብከት የአቢ ደንጎሮ ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት መልአከ ገነት ቀሲስ ደመቀ ታደሰ በበኩላቸው በወረዳቸው ‹‹ኦነግ ሸኔ›› የተባለው ታጣቂ ቡድን ሃይማኖት ተኮር ጥቃት እንደፈጸመ ተናግረው በጥቃቱም በርካታ ካህናት፣ ዲያቆናት መምህራንና ምእመናን እንደተገደሉ አረጋግጠዋል። ታጣቂ ኃይሉ መጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጸሎት ላይ የነበሩ አገልጋዮች ካህናትንና ምእመናንን ከገደለ በኋላ በየመንደሩ እየዞረ የቀሩትን ኦርቶዶክሳውያን እንደገደለ ኃላፊው አስረድተው አስከሬናቸው የተገኘ ፲፱ ሰዎች ብቻ ተቀብረዋል›› ሲሉ ተናግረዋል። የሟቾች ቁጥር እስከአሁን ድረስ ፲፱ ይባል እንጂ ፳፪ እና ከዚያ በላይ ሊሆን እንደሚችል ኃላፊው ተናግረው ከተገደሉት በተጨማሪም በርካቶች ታፍነው እንደተወሰዱ አስረድተዋል። የምእመናን ሀብት ንብረት እንደተዘረፈና ቤታቸው እንደወደመም ገልጠዋል።

ጥቃቱ የተፈጸመው የካቲት ፲፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ቅዳሜ ከቀኑ ሰባት ጀምሮ እንደሆነ የጠቆሙት ኃላፊው ቤተሰቦቻቸው የተገደሉባቸውንና ታፍነው የተወሰዱባቸውን ሕፃናት ከነ ነፍሳቸው በአቅራቢያ በሚገኝ ወንዝ ላይ እንደጣሏቸው አስረድተዋል። በወቅቱ ግማሽ የሚሆነው የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ወደ ገቢያ በመሄዱ ቀሪዎቹ አቅም ኖሯቸው ታጣቂ ኃይሉን መመከት እንዳልቻሉ ያነሡት ኃላፊው የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ በርካታ ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ እንደተገደሉ አስረድተዋል። አስክሬናቸው እስከአሁን ድረስ ያልተገኘ እንዳለም አክለው ተናግረዋል።

በወረዳው ሥር ፴፮ አጥቢያዎች የሚገኙ ሲሆን በአካባቢው የሚኖረው አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍሎች የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መሆናቸው ታውቆ ጥቃቱ እንደተፈጸመ ያስረዱት ኃላፊው ጥቃቱ ከተፈፀመ በኋላ የተረፉ ምእመናን ተሰብስበው ራሳቸውን ለመከላከል ጥረት ቢያደርጉም ‹‹የኦነግ ሸኔ›› ታጣቂ ኃይል ትጥቅ ከሕዝበ ክርስቲያኑ አቅም በላይ በመሆኑ ለከፋ የጸጥታ ችግርና ለሕይወት መጥፋት እንደተዳረጉ ተናግረዋል። የአካባቢው የመንግሥት ታጣቂ ኃይልም ‹‹የኦነግ ሸኔ›› ታጣቂ ኃይል ደጋፊና መረጃ አቀባይ በመሆኑ ለእነርሱ ችግራቸውን ማስረዳትም ሆነ እገዛ መጠየቅ የማይታሰብ መሆኑን ኃላፊው አስረድተዋል።

አንዳንዴ በአካባቢው ችግር እንዳለ መረጃ ደርሷቸው የፌዴራል የፀጥታ ኃይሎች በቦታው ተገኝተው ማጣራት ሲፈልጉ የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት ችግር እንደሌለ ነግረዋቸው እንደሸኛቸው ያረጋገጡት ኃላፊው “ይህም በመሆኑ የአካባቢው ኅብረተሰብ ለከፋ የፀጥታ ችግር ከመጋለጡ ባሻገር ሕይወታቸውን ሙሉ በሥጋት እንዲያሳልፉ አድርገዋቸዋል” ብለዋል። ባለሥልጣናቱም ለታጣቂ ኃይሉ ሽፋንና የስንቅና ትጥቅ አቅርቦት ከማድረግ ውጭ ለንጹሓን የአካባቢው ኗሪ ምንም ዓይነት የሕግ ከለላ አያደርጉላቸውም ሲሉም ተናግረዋል። ታጣቂ ቡድኑ ካህናትንና ምእመናንን እየመረጠ የገደለ ሲሆን “ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ካቃጠልን ድጋሜ ሊሠሩ ይችላሉ፣ ካህናትና መምህራንን ቀድመን ካጠቃን ግን የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ያበቃል›› በሚል እሳቤ ተነሳስቶ ጥቃት ሲፈጽም እንደነበረም ኃላፊው ተናግረዋል። ጉዳዩን ከወረዳ እስከ ዞን ላሉ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ናትናኤልና በሥራ አስኪያጁ በኩል እንዳስረዱ ኃላፊው አክለው ገልጠዋል።

የአቢ ደንጎሮ ወረዳ አስተዳዳሪ አቶ ብሪሳ ኃይሌ ጉዳዩን አስመልክቶ ለተነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ማብራሪያ

በወረዳቸው የሚንቀሳቀሰው ‹‹ኦነግ ሸኔ›› የተባለው ታጣቂ ቡድን በንጹሓን ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ አሰቃቂ ጥቃት መፈጸሙን ተናግረው “በአካባቢው በቂ ጥበቃ አሰማርተን ንጹሓንን ስንጠብቅ የነበረ ቢሆንም ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ግን ጥቃቱ ተፈጽሟል” ብለዋል:: ዕለቱ የገበያ ቀን በመሆኑም በጥበቃ ላይ የነበሩ አንዳንድ የአካባቢው የፀጥታ ኃይላት ወደሌላ አካባቢ መንቀሳቀሳቸውን ተከትሎ የተፈጸመ ጥቃት እንደሆነም ኃላፊው አስረድተው:: “ጥቃቱ የተፈጸመበት አካባቢ ከወረዳቸው ርቀው ጫካ አካባቢ በሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ እንደሆነ የገለጡት አስተዳዳሪው ይህም ከርቀቱ አንጻር ደኅንነታቸውን የመጠበቁን ሥራ አክብዶብናል” ብለዋል:: በወቅቱ ጥቃቱን ያደረሰው ታጣቂ ቡድንም የጥቃቱ ሰለባዎች መረጃ እንዳያወጡ በሚል ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን እየነጠቀ እንደገደላቸው አስተዳዳሪው ተናግረዋል::

ታጣቂ ቡድኑ አንድ ቦታ ላይ ሆኖ መዋጋት የማይችልና አሳቻ ሰዓት ጠብቆ ሕዝብን ጨፍጭፎ የሚሠወር ኃይል ነው ያሉት አስተዳዳሪው “ይህም ንጹሓንን ከጥቃት ለመከላከል ፈታኝ አድርጎታል” ብለዋል:: ዘላቂ ሰላም በአካባቢው ማስፈን የሚቻለው የአካባቢውን ኅብረተሰብ በዘላቂነት ማደራጀት እንደሆነ አስተዳዳሪው ጠቅሰው “የአካባቢው ኅብረተሰብ ታጥቆ ራሱን እንዲከላከል የማድረግ ሥራ ስንሠራ ቆይተናል፤ ለወደፊቱም አጠናክረን እንቀጥላለን” ሲሉ አስረድተዋል:: “በአሁኑ ወቅት በቂ የሚባል የፀጥታ ኃይል በአካባቢው ላይ በመሠማራቱ አካባቢው የተረጋጋ ሆኗል” ብለዋል”:: ጥቃት የተፈጸመባቸው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መሆናቸውን አስተዳዳሪው አስረድተው የሟቾች ቁጥርም ሃያ ሁለት ብቻ እንደሆነም ተናግረዋል::

ጥቃቱን ሸሽተው ከተሰደዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት አድርገን ወደ አካባቢያቸው የሚመለሱበትን ነገር እያመቻቸን እንገኛለን ያሉት አስተዳደሪው የተሰደዱት ወደ አካባቢያቸው ከተመለሱ በኋላ ውይይቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን በቀጣይም ዘላቂ ሰላም በሚመጣበት ዙሪያ አቅጣጫ በጋራ እናስቀምጣለን ሲሉ ተናግረዋል:: በታጣቂዎች ታፈነው ከተወሰዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሦስት ያህሉን ማስመለስ እንደቻሉም አስተዳዳሪው ለዝግጅት ክፍላችን አስረድተዋል::

በአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት ቀርበው በስልክ አስተያየታቸውን የሰጡት የአካባቢው ኗሪ ታጣቂ ቡድኑ ጥቃቱን የጸፈመው የካቲት ፲፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ቅዳሜ ዕለት ከቀኑ ሰባት ሰዓት ጀምሮ እንደሆነ ተናግረው ታጣቂ ቡድን በአካባቢው በሚገኘው መንደር እየዞረ ያገኘውን ሰው ወደ ኋላ በገመድ እያሰረ እንዳረዳቸው አስረድተዋል:: በጥቃቱ አረጋውያን ጨምሮ ሕፃናት የታረዱ ሲሆን በተለይ ፲፱ የሚሆኑትን በኋላቸው አስሮ አርቆ በመውሰድ አርዶ እንደገደላቸው ያዩ መሆኑን ለቴሌቭዥን ጣቢያው በስልክ ተናግረል::

“ኦነግ ሸኔ” የተባለው ታጣቂ ቡድን በተለየ ሁኔታ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖችን እያጠቃ መሆኑን ያስረዱት ግለሰቡ የወረዳው የፀጥታ ኃይልም ለታጠቂ ቡድኑ እገዛ እንደሚያደርግለት ተናግረዋል:: የአካባቢው ኅብረተሰብ በዚህ ወቅት ወደ መኖሪያ ቀዬው እንዳልተመለሰና ምግብ ለመብላት ብቻ ወደ አካባቢያቸው ዘልቀው ከሰዓት በኋላ ደግሞ ወደ ጫካ ተመልሰው እንደሚሄዱ አያይዘው አስረድተዋል:: እስካሁን ድረስም ወደ አካባቢያቸው መመለስ ባለመቻላቸው ሀብት ንብረታቸው በታጣቂ ቡድኑና በተባባሪዎቹ እየተዘረፈባቸው እንደሆነ ግለሰቡ አስረድተዋል::

**ጥቃቱን ሸሽተው ከተሰደዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት አድርገን ወደ አካባቢያቸው የሚመለሱበትን ነገር እያመቻቸን እንገኛለን ያሉት አስተዳደሪው የተሰደዱት ወደ አካባቢያቸው ከተመለሱ በኋላ ውይይቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን በቀጣይም ዘላቂ ሰላም በሚመጣበት ዙሪያ አቅጣጫ በጋራ እናስቀምጣለን ሲሉ ተናግረዋል።**



ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ

# ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ
# ከ፲፱፻፳፩ - ፲፱፻፹፩ ዓ.ም

## በመጽሐፈ ሲራክ

*ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የብዙ ሊቃውንት አባቶች መፍለቂያ ምንጭ ናት:: ሰማዕታትን፣ ደናግላኑን ሐዋርያትን፣ ጻጻሳትን፣ መነኮሳትን፣ ያፈራች የቅዱሳን እናት ናት:: ብዙዎቹ በተሰጣቸው ዘመን ወደዚህ ዓለም መጥተው በቅድስና በንጽሕና ኖረው፣ አስተምረው፣ጸልየው፣ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ለቤተ ክርስቲያን ክብር ቆመው እና አገልግለው በስተመጨረሻም ዘመን ገቷቸው አንቀላፍተዋል::*

*በዘመናቸው ተነስተው እንደ ተወርዋሪ ኮከብ አብርተው፣ መልካም ገድልን በመጋደል እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ሩጫቸውን ጨርሰው በገነት ወደ ቅዱሳን ማኅበር ከተቀላቀሉት መሀከል ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ አንዱ ናቸው:: እኛም የብፁዕነታቸውን የሕይወት ታሪክ፣ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን ባጠቃላይ እስካረፉበት መጋቢት ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ያለውን ዜና ሕይወታቸውን በሚከተለው መልኩ አቅርበነዋል መልካም ንባብ፦*

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በቀድሞ ስማቸው አባ ጸጋዬ ቢሆነኝ በዚያን ጊዜ አጠራር በደቡብ ጎንደር አስተዳደር በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ልዩ ስሙ ቆማ ፋሲለደስ ተብሎ በሚታወቀው ታላቅ ገዳም ከአባታቸው ከቀኝ ጌታ ቢሆነኝ ዋሴ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ውዴ መሸሻ በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ተወለዱ::

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በመካነ ልደታቸው በቆማ ፋሲለደስ ፊደል፤ ዳዊትና ጸዋትወ ዜማ ከታወቁት ከታላቁ የቆሜ ድጓ ምሥክር ከነበሩት ከመምህር ሐዲስ ተምረዋል:: በጥር ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣትም ከግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ ከአቡነ ቄርሎስ ማዕረገ ዲቁናን ተቀበሉ::

ብፁዕነታቸው የቀድሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን ፈለግ በመከተል መንፈሳዊ ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት በነበራቸው ጽኑዕ ፍላጎት ከትውልድ ቦታቸው ወጥተው በልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገራት በመዘዋወር ከአያሌ ኢትዮጵያውያን መምህራን የቤተ ክርስቲያችንን ከፍተኛ ትምህርት በመቅሰም መንፈሳዊ ዕውቀትን ገብይተዋል::

በዚሁ መሠረት ከደቡብ ጎንደር ወደ ምሥራቅ ጎጃም ሄደው በሞጣ አውራጃ ድቦ ኪዳነ ምሕረት ቅኔ እስከነአገባቡ ተምረዋል:: ወደ ደቡብ ጎንደር በመመለስም በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ ደብረ ዕንቍ ከመምህር ጌጡ ተሰማ ተጨማሪ የቅኔ ትምህርታቸውን አስፋፍተዋል::

ቀጥሎም ወደ ደቡብ ወሎ በመሄድ በአማራ ሳይንት ወረዳ፤ በሮ ሚካኤል ከነበሩት ከአለቃ ከበደ የቅኔ ትምህርትን ከነአገባቡ በመማር አጠናቀው በመምህርነት ተመርቀዋል:: በመጻሕፍት ትርጓሜ ረገድም በዚያው በቦረና ሣይንት አውራጃ በመካነ ሰላም ከአለቃ ታመነ አግደው ትርጓሜ ነገሥትን፣ በደሴ አውራጃ በደሴ መድኃኔ ዓለም ከአባ

ገብረ ማርያም ገብረ ሐና ዳዊትን፣ የውዳሴና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜን ከመምህር ገብረ እግዚአብሔር ሐጎስ የትምህርተ ኅቡአት ፣ የኪዳንና የፍትሐ ነገሥት ትርጓሜን ተምረዋል። ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በደቡብ ወሎ በትምህርት ላይ ነበሩበት ጊዜም በ፲፱፻፵ ዓ.ም በታላቁ ገዳም በደብረ ሊባኖስ ሕገ ምንኩስናን ተቀብለዋል። መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ.ም በግሼን ማርያም ማዕረገ ቅስናን ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል የጎንደር ሊቀ ጳጳስ ተቀብለዋል።

ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በታዕካ ነገሥት በዓታ መታሰቢያ ቤት የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርታቸውን ቀጥለው ሐዲሳትን ከመምህር ገብረ ሕይወትና ከመምህር ሥምረተ አብ ቀጸላ፣ ብሉያትን ከመምህር ጌራ፣ አቡሻህርን ደግሞ ከመምህር ገብረ ሕይወትና ከመምህር ኪዳነ ማርያም ተምረው ተመርቀዋል።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ከፍ ብሎ በዝርዝር እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ባህል እውነተኛ ምንጮች ከሆኑት ኢትዮጵያውያን መምህራን ነገረ መለኮትን አጥንተው ካስመሰከሩ በኋላ በመምህርነት ተመርቀዋል።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በተለያዩ ሊቃውንት የቤተ ክርስተያንን ዕውቀት ከቀሰሙ በኋላ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ በሐዲሳት ትርጓሜ መምህርነት ተመድበው እስከ ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ድረስ ለዐሥራ አምስት ዓመታት ያለማቋረጥ በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል። ከዚህም በተጨማሪ የካቴድራሉ ቄሰ ገበዝ በመሆን መንፈሳዊ ፍቅርን በተሞላ ሰብእና ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል።

በተጨማሪም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት በአስተማሪነት ተመድበው ብዙ ወጣቶችን አፍርተዋል። ቀደም ሲል ማኅበረ እስጢፋኖስ ሲባል የነበረው የካህናት ማኅበር እንዲሁም ማኅበረ ሥላሴ እየተባለ ይጠራ በነበረው የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ዘወትር ቅዳሜና እሑድ በመገኘት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና ነገረ መለኮትን በማስተማር ከፍ ያለ አገልግሎት ሰጥተዋል። በተለይም የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች በሚያደርጉት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሁሉ በመሳተፍ በማኅበሩ ውስጥ እየተመረጡና እያስተማሩ ለማኅበሩ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች አበርክተዋል።

ቅዱስ ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በነበራት ሰፊ እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያንዋ ለምትጠብቀው አገልግሎት አዳዲስ ኤጲስ ቆጶሳት እንዲመረጡ በተወሰነው መሠረት ጥር ፫ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም ከተመረጡት ፲፫ ኤጲስ ቆጶሳት መካከል ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ አንዱ ሆነው በመመረጥ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ማዕረገ ጵጵስናን ተቀብለዋል።

ማዕረገ ጵጵስናን እንደተቀበሉ በቀድሞው የኤሊባቦር ክፍለ ሀገር ኤጲስ ቆጶስ ሆነው በመሾም በሀገረ ስብከቱ የተለያዩ መንፈሳዊ ተግባራትን አከናውነዋል። ከነዚህ መንፈሳዊ ተግባራት መካከልም ፦ በዚሁ በተመደቡበት ኤሊባቦር ልዩ ስሙ ዳበና በተባለው ሥፍራ ፪፫ ኪሎ ሜትር መንገድ በእግራቸው በመጓዝ እና በማስተማር ለካህናት ማሰልጠኛ መጠናከር አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ብፁዕነታቸው በዚሁ ሀገረ ስብከት በነበራቸው መንፈሳዊ አገልግሎት ሰበካ ጉባኤ አደራጅተዋል፣ ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን አቋቁመዋል፣ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በማቋቋም እናት እና አባት ለሌላቸው ልጆች ምግብ፣ መጠለያ እና ትምህርት እንዲያገኙ አድርገዋል። የመቱ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን ለሀገረ ስብከቱ በሚመጥን መልኩ በካቴድራል ደረጃ ከፍ አድርገው አሠርተዋል። ከዚህም በተጨማሪ የሰንበት ትምህርት ቤትን በማቋቋምና በማደራጀት ብዙ ወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት አባል ሆነው ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ አድርገዋል።

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በጥር ወር ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የኤርትራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ተዛውረው ከሄዱበት ጊዜ ጀምሮ በሀገረ ስብከቱ ዘርፈ ብዙ መንፈሳዊ አገልግሎት ሰጥተዋል። በተለይም ለቤተ ክርስቲያን እድገትና የካህናትን ኑሮ ለማሻሻል በወጣው ቃለ አዋዲ መሠረት ለምእመናን ጥቅሙን በማስረዳትና የነበረውን ችግር በማስወገድ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰበካ ጉባኤ አስጀምረዋል።

ብፁዕነታቸው በሀገረ ስብከቱ የካህናት በጀት እንዲከፈት

በማድረግ በየወረዳው ሊቃነ ካህናትን መድበዋል:: በተጨማሪም ለካህናትና ለመምህራን ለቢሮ ሠራተኞች ደሞዝ እንዲሻሻል በከፍተኛ ጥረት አዲስ በጀት አስከፍተዋል:: የአስመራ አብያተ ክርስቲያናትን በማስተባበርም በሰበካ ጉባኤ ገቢ ላይ ገንዘብ እንዲዋጣና ከሀገረ ስብከቱም ወጭ በማድረግ ለሠልጣኝ ካህናት ለትራንስፖርትና ለመምህራን አበል በመክፈል ራስ አገዝ የካህናት ማሠልጠኛ ከፍተው ካህናቱ በየሦስት ወሩ እንዲሠለጥኑ አድርገዋል:: በሀገረ ስብከቱ ብዙ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ ፣ብዙ ዘመን የቆዩትም በአዲስ መልኩ እንዲሠሩ አድርገዋል::

ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ወደ ጎንደር ሀገረ ስብከት እስከተዛወሩበት የጥቅምት ወር ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኤርትራ ክፍለ ሀገር በድርቅና በሰላም መታጣት ችግር ላይ ለወደቁ ወገኖች የምታከናውነውን የርዳታ ሥራ ሲመሩና ሲያስተባብሩ ቆይተዋል::

**ብፁዕነታቸው በዚሁ ሀገረ ስብከት በነበራቸው መንፈሳዊ አገልግሎት ሰበካ ጉባኤ አደራጅተዋል፣ ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን አቋቁመዋል፣ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት በማቋቋም እናት እና አባት ለሌላቸው ልጆች ምግብ፣ መጠለያ እና ትምህርት እንዲያገኙ አድርገዋል። የመቱ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን ለሀገረ ስብከቱ በሚመጥን መልኩ በካቴድራል ደረጃ ከፍ አድርገው አሠርተዋል።**

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አማካኝነት የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲሠሩ ተመድበው በሀገረ ስብከቱ ሥራ በጀመሩ በአራት ወራት ውስጥ ብዙ የትሩፋት ሥራዎችን አከናውነዋል:: በጎንደር ከተማ አዘዞ ሚካኤል የሚገኘውን የካህናት ማሠልጠኛ በቦታው ድረስ እየተገኙ በማስተማር ከማበረታታቸውም በላይ ማሠልጠኛውን በገንዘብ ይደግፉ ነበር::

የጉባኤ ቤቶች ተጠናክረው እንዲስፋፉ በነበራቸው ጽኑዕ ዓላማ መሠረት በጎንደር ከተማ ውስጥ ለተለያዩ ጉባኤ ቤቶች ከግል ገንዘባቸው ልግስና አድርገዋል:: ለድሆች፣ ለጦም አዳሪዎች ከግል ገንዘባቸው ችሮታ ሲያደርጉ ቆይተዋል:: በየአውራጃው እየተዘዋወሩ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲጠገኑ ሐሳብና መመሪያ ሰጥተዋል:: በተለይም የቆማ ፋሲለደስ ገዳም እንዲታደስና ቆርቆሮ እንዲለብስ አስፈላጊውን ገንዘብና ቁሳቁስ እንዲያገኝ ከፍተኛ የማስተባበር ተግባር ፈጽመዋል::

በጎንደር ደብረ ታቦርና በወረታ ያሉትን የሕፃናት ማሳደጊያዎች ተዘዋውረው በመጎብኘት ለሕፃናት ትምህርትና ምክር በመስጠት የሕፃናት ማሳደጊያዎቹም የበለጠ እንዲስፋፉ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በደብረ ታቦር የሚገኙትን የችግኝ ጣቢያዎች ተዘዋውረው በመጎብኘት ብዙ የድጋፍ ሥራን ሠርተዋል:: በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዝናብ እጥረት ችግር የደረሰባቸውን ወገኖች ለመርዳት በሌቦ አውራጃ በአዲስ ዘመን እና በእብናት ያቋቋመቻቸውን ሦስት የርዳታ ጣቢያዎች በመጎብኘት እና የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴውን በመከታተል ለተጎዱ ወገኖች ርዳታ እንዲያገኙ የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል::

ብፁዕነታቸው በሕይወተ ሥጋ በነበሩባቸው ዓመታት ሁሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በቅንነት ሲያገለግሉ የቆዩ ፤ለብዙዎች አርአያ የሆኑ መንፈሳዊ አባት ነበሩ:: ሀብተ ክህነት፣ሀብተ ትሕትና፣ ሀብተ ጾም፣ ሀብተ ጸሎት፣ ሀብተ ፍቅር እንዳላቸው በብዙዎች ዘንድ የሚነገርላቸው ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ባደረባቸው ሕመመም ምክንያት በተወለዱ በ፷፩ ዓመታቸው መጋቢት ፲፺ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሥጋ አርፈዋል:: ብፁዕነታቸው ከዚህ ዓለም በሥጋ ቢለዩም በመንፈስ ሕያው ሆነው ይኖራሉ::

*በረከታቸው ይደርብን*

# “ሀገራዊ ምርጫው በብሔርና በሃይማኖት ምክንያት በኢትዮጵያውያን መካከል የተፈጠረውን ቁርሾ የሚያጠፋ ሊሆን ይገባል”

*ብፁዕ አቡነ አረጋዊ ዶ/ር*
*(የጅቡቲና ድሬደዋ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና*
*በቅዱስ ፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት የውጭ ጉዳይ ግንኙነት ኃላፊ)*



ብፁዕ አቡነ አረጋዊ ዶ/ር

በካሣሁን ለምለሙ

*በዓለማችን ያሉ ብዙ ሀገራት በየአራት ወይም በየአምስት ዓመታት ልዩነት ሀገራዊ ምርጫ ያካሄዳሉ። በየሀገራቱ ያሉ ሕዝቦችም “ይበጀናል ለውጥ ያመጣልናል” ያሉትን የፖለቲካ ድርጅት በካርዳቸው አማካይነት ይመርጣሉ። የፖለቲካ ድርጅቶችም ከምርጫው ጊዜ ቀደም ብሎ “ሕዝብን ያሳምንልናል፤ እንድንመረጥ ያግዘናል” የሚሉትን የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም በዐደባባይ ወጥተው ያስተዋውቃሉ። አንዳንዴ በዚህ ሂደት ውስጥ አልፎ ምርጫው በሰላም መጠናቀቁና በምርጫው አሸናፊ የሆነውን አካል እንኳን ደስ አለህ/ አለሽ ተባብሎ የመለያየቱ ጉዳይ ግን አሳሳቢ ይሆናል። በምርጫ ወቅት የሰው ሕይወት ይጠፋል፤ ሀብት ንብረት ይወድማል፤ የሀገር ሉዓላዊነትም አደጋ ላይ ይወድቃል።*

*በተለይ በአፍሪካና በአንዳንድ ታዳጊ ሀገራት ሀገራዊ ምርጫ ያለስጋትና ያለፀጥታ ችግር የሚጠናቀቅባቸው ጊዜያት ውስን ይሆናሉ። በሀገራችን ባለፉት አምስት ዙር የተካሄዱት ሀገራዊ ምርጫዎች ለፀጥታ ችግር የተጋለጡ ሆነው አልፈዋል። በምርጫዎቹ ወቅት የሰው ሕይዎት ያለአግባብ የጠፋበት፤ በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በአንዳንድ ዕብሪተኛ የፖለቲካ ኃይሎች ሥርዓቷ፣ቀኖናዋ፣ዶግማዋ፣ክብሯና መብቷ የተጣሰባቸው ዓመታትን አሳልፈናል። ላለፉት ሠላሳ ዓመታት በሀገሪቱ የነበረው የፖለቲካ ኃይል በስሑት ትርክት ተነሣሥቶ ቤተ ክርቲያንን “በጠላትነት” በመፈረጅ እውነተኛ አገልጋይ አባቶችና ምእመናን ተሸማቀው እንዲኖሩና በእምነታቸው እንዲያፍሩ ሲደርግ ቆይቷል።*

*በየአምስት ዓመቱ የሚካሄደውን ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ በሀገራችን ኢትዮጵያ ስድስተኛውን ሀገራዊ ምርጫ ለማካሄድ ምርጫ ቦርድ መርሐ ግብር አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችም በዚህ ወሳኝ ሀገራዊ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ በየዐደባባዩ እየዞሩ ፖለቲካዊ አማራጭ ሐሳባቸውን በማስተዋወቅ ላይ ይገኛሉ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንም የሀገሪቱ አካል ናቸውና በምርጫው ወቅት ሊኖራቸው ስለሚገባው ድርሻ አስመልክቶ ከጅቡቲና ድሬደዋ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት የውጭ ጉዳይ ግንኙነት ኃላፊ ከሆኑት ብፁዕ አቡነ አረጋዊ ዶ/ር ጋር ያደረግነውን አጭር ቆይታ በሚከተለው መልኩ አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።*

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በሀገሪቱ ሊካሄድ የታሰበው ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ በምን ሁኔታ ሊከናወን፣ በምርጫው ወቅትስ ምእመናን ምን ዓይነት ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል ይላሉ?

***ብፁዕ ዶ/ር አቡነ አረጋዊ፡-*** ሀገራዊ ምርጫ ማለት ሕዝብን ለማስተዳደርና ለመምራት የሕዝብን እውነተኛ ድምፅ ለማግኘት የሚካሄድ አንድ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው:: የሀገራዊ ምርጫ ዋናው ግብ ሕዝባዊ ይሁንታን አግኝቶ ሀገርንና ሕዝብን መምራት ነው:: በሀገራዊ ምርጫ ወቅት ገዥው የፖለቲካ ድርጅትና ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች የየራሳቸውን ሐሳብ ለኅብረተሰቡ በመግለጽ የፖለቲካ መንበርን የሚይዙበት ሂደትም ነው:: ስለዚህ በሀገራችን ሊደረግ በሂደት ላይ ያለው ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ሰላማዊና ፍትሐዊ እንዲሆን እንመኛለን::

ምርጫው የኢትዮጵያዊነትን ዕሴት፣ አንድነት፣ ፍቅርንና መተሳሰብን የሚሸረሽር ሆኖ መከናወን የለበትም:: የፖለቲካ ድርጅቶች አለን የሚሉትን አማራጭ ሐሳባቸውን ለኅብረተሰቡ በመግለጽ በፍትሐዊነት የመንግሥትን መንበረ ሥልጣን የሚይዙ፤ የሀገርን ሰላምና ዕድገት ለማሻሻል ጥረት የሚያደርጉ መሆን አለባቸው:: ሀገራዊ ምርጫው በብሔርና በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት በኢትዮጵያውያን መካከል የተፈጠረውን ቁርሾና የኢኮኖሚ ውድቀት የሚያስወግድ ምርጫ ሊሆን ይገባል:: በሕዝቦች መካከል ጠብ የሚዘሩና መለያየትን የሚሰብኩ አካላት ጭምር ሥርዓት የሚይዙበትና ሀገራችን ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ኃያልነቷ ተመልሳ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ብቻ ሳትሆን ለሌሎች ክፍላተ አህጉር ምሳሌ የሆነ ሀገራዊ ምርጫ እንዲካሄድባትም የሁሉም ፍላጎት ሊሆን ይገባል::

የሃይማኖት ተቋማት ነፃነት ተከብሮ ሰው በፈለገው ቦታ ሆኖ ማምለክ የሚችልበት ዘመን እንዲመጣ እንመኛለን:: በተለይ ከዚህ ቀደም የነበረው መንግሥታዊ ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን የተበደሉበትና የተገፉበት ሥርዓት ነበር:: አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች በስሑት ትርክት ተነሣሥተው ቤተ ክርስቲያንን "በጠላትነት" ከመፈረጅ ባሻገር "የጭቆና፣ የድህነትና የኋላ ቀርነት" ምሳሌ አድርገው ሲያቀርቧት ይስተዋሉ ነበር:: ይህ ግን የተሳሳተ፣ ቤተ ክርስቲያን ለሀገርና ለወገን የከፈለችውን ታላቅ ዋጋ የካደ ልዕልናዋንም ያላከበረ ትርክት ነው::

በመጭው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ተወዳድረው የሚያሸንፉ የፖለቲካ ድርጅቶች የተሳሳቱ ትርክቶችን የሚያርሙና ቢቻል በስሑት ትርክት ምክንያት ላለፉት ፵ ዓመታት ጉዳት የደረሰባትን ቤተ ክርስቲያን የሚክሱና ይቅርታ መጠየቅ የሚችል ቅን ልቡና ያላቸው መሆን አለባቸው:: በዚህ ዘመን ያለን ሕዝበ ክርስቲያንም የስሑት ትርክት ማወራረጃ መሆን እንደሌለብን ጠንቅቀን በማወቅ በስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ለመሳተፍ የሚያበቃንን ካርድም በመውሰድ በግብታዊነት ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያናችንና ለምእመናን የሚጠቅመውን የፖለቲካ ድርጅት መምረጥ ይጠበቅብናል::

በሀገራችን ለምርጫ ውድድር የቀረቡት የፖለቲካ ድርጅቶች የሚያቀርቡትን ፖለቲካዊ አማራጭ ሐሳብ ምእመናን በትክክል መረዳት ይጠበቅባቸዋል:: ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ይበጃል የሚሉትን ከመምረጥ ባሻገር በምርጫው ወቅት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማገዝና ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል:: የዘመኑ አሰላለፍ መቀየሩን አውቀን ህልውናችንን ሊያስጠብቅልን የሚችለውን የፖለቲካ ድርጅት መምርጥ የማንችል ከሆነ ዘላለም የችግር ሁሉ ገፈት ቀማሽ፤ አቤቱታ አቅራቢና ኀዘንተኞች እንሆናለን:: ለኀዘናችን ማስታገሻ ስንልም በእምነትና በምግባር ለማይመስለን መንግሥት "ተገፋን" ብለን ድምጻችን ስናሰማ ለሀገር ከምናበረክተው ድርሻ እንወጣለን::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ቤተ ክርስቲያን የተከፈተባትን ስሑት ትርክት ለማረም፤ የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ደኅንነትም ለማስጠበቅ ስለ መጪው ሀገራዊ ምርጫ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ቅድመ ዝግጅት እያደረገች ነው?

***ብፁዕ ዶ/ር አቡነ አረጋዊ፡-*** ቤተ ክርስቲያንን በስሑት ትርክት የመወንጀል ምንጬ ምዕራባውያን ናቸው:: ቤተ ክርስቲያን ሀገር መሆኗንና በአድዋ ድል ላይ ያበረከተችውን አስተዋጽኦ ስለሚያውቁ ያን መበቀል ይፈልጋሉ:: ለሀገር ውስጥ ፀረ-ኦርቶዶክስ ኃይላት የገንዘብ ድጎማ በማድረግ ጭምር ቤተ ክርስቲያንን በስሑት ትርክት የመወንጀል ሥራ ይሠራሉ:: በመሆኑም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ማስተዋል አለባቸው፤ የስሑት ትርክት ምንጬ የትና እነማን መሆናቸውን በመለየት ለእርሱ የሚሆን ስልት

መንደፍ አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያን ለሀገር ግንባታና አንድነት ትልቅ ሚና እንደተጫወተች ምእመናንም ሆኑ የመንግሥትን የሥልጣን መንበር የሚይዙ አካላት ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል:: ሆን ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሲነዙ የነበሩ የሐሰት ትርክቶች የቤተ ክርስቲያንን ታላቅነት ከግምት ውስጥ ያላስገቡና የኢትዮጵያንም ሉዓላዊነትና ነፃነት ለመናድ የሚቀነቀኑ ሴራዎች ነበሩ::

የቤተ ክርስቲያን ኃያልነትና ለሀገር ያበረከታችው አስተዋፅኦ አንድ ቀን ይገለጣል፤ ዓለምም ዐይኑን ገልጦ ልቡናውንም ከፍቶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በሙሉ ልቡ ይቀበላታል:: ቤተ ክርስቲያን ፍትሐዊነትን ያስተማረችና ድኃ እንዳይበደል ፍትሕ እንዳይጓደል ጠንክራ የሠራች ናት:: ቤተ ክርስቲያን ለሀገርና ሕዝብ ጠቃሚ የሆነችና ለአፍሪካ ጥቁር ሕዝብም የነፃነት ፋና ወጊ የሆነች እንዲሁም ለዓለም ሕዝብ ታሪክን፣ ቅርስንና ሃይማኖትን ጠብቃ ያቆየች ናት:: የሀገራችን የማኅበረሰብ አንቂዎችም ሆኑ የፖለቲካና የታሪክ ምሁራንም ይንን ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ተረድተው ለእውነት መቆም አለባቸው::

ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ጊዜ የሐሰት ትርክት ሰለባ ብትሆንም ክብሯና ለሀገር የምታበረክተው ድርሻ አይቀንስም:: ሰዎች ዓይናቸውን ገልጠው እስኪያዩ ድረስ እውነቱን በተገቢ መንገድ ማስረዳት የእኛ አባቶች ድርሻና የምእመናን ሊሆን ይገባል:: ከዚህ ቀደም ቤተ ክርስቲያን የነበራትን ሀገራዊ ድርሻ ለማስቀጠል መጪው ሀገራዊ ምርጫ ፍትሓዊና በሕዝብ ዘንድ ተአማኒ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የድርሻዋን ትወጣለች፤ ምእመናንዋም በድጋሜ ዋጋ እንዳይከፍሉ በምርጫው ወቅት በጥንቃቄ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ትመክራለች::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ሕልውና አስመልክቶ በሀገሪቱ ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ውይይት አለ?

***ብፁዕ ዶ/ር አቡነ አረጋዊ፡-*** እስካሁን ድረስ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ሕልውና አስመልክቶ በሀገሪቱ ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የተደረገ ምንም ዓይነት ውይይት የለም:: ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ድርጅቶችን ጠርታ ማነጋገሩ ጠቃሚ ነው ብላ ባለማመኗ ውይይት አላደረገችም:: ነገር ግን በምርጫ ወቅት የምርጫ ሕጎችና ደምቦች እንዳይጣሱ፣ የሰው ሕይወት እንዳይጠፋ፣ ንብረት እንዳይወድምና የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና አንድነት የሚሸረሽሩ ጉዳዮች እንዳይከሠቱ ቤተ ክርስቲያን የመካሪነትና የአስተማሪነት ድርሻዋን በሚገባ ትወጣለች::

የፖለቲካ ድርጅቶች የሕዝብን ደኅንነት በጠበቀ መልኩ መጭውን ምርጫ እንዲያካሂዱ ቤተ ክርስቲያን ትመክራለች:: ለምእመናንም ያመኑበትንና መብታቸውንና ጥቅማቸውን ሊያስከብርላቸው የሚችለውን የፖለቲካ ድርጅት እንዲመርጡ ቤተ ክርስቲያን ጥሪ ታስተላልፋለች፤ እንዲሁም በምርጫው ወቅት ከሁከትና ብጥብጥ እንዲቆጠቡና ከግርግር እንዲርቁ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የቤተ ክርስቲያን ልጆች በሀገሪቱ የፖለቲካ ሱታፌ ውስጥ የፖለቲካ ውክልና የማያገኙት ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ተሳትፎን "በመጥፎ ስላ ስለምትመለከተው ነው" ይባላልና በዚህ ላይ ምን ሐሳብ አለዎት?

***ብፁዕ ዶ/ር አቡነ አረጋዊ፡-*** ይህ ሐሳብ ከእውነታው ጋር በተቃርኖ የቆመ ነው:: በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ ከነበሩ መንግሥታት ጋር ትወግን ነበር ይባላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ልጆቿ የፖለቲካ ውክልና እንዳይኖራቸው ክልከላ አድርጋለች ይባላል:: እውነታው ግን ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳያደርጉ አልከለከለችም፤ ከልክላም አታውቅም:: የፖለቲካ ተሳትፎንም በጎ ባልሆነ ዕይታ ቃኝታ አላስተማረችም:: ሰዎች የፖለቲካ ተሳትፎን በራሳቸው ምክንያት ሸሽተው ‹‹ቤተ ክርስቲያን ናት የከለከለችን›› ብሎ ማቅረብ ፍጹም ስሕተት ነው:: ከዚህ በኋላ ሁላችንም ፖለቲካን የምናይበት ዕይታ የተስተካከለ መሆን አለበት:: ፖለቲካን አስፈሪ በሆነ መንገድ መመልከት መቆም አለበት::

በአሁኑ ሰዓት መብትንና ጥቅምን ለማስከበር የግድ የፖለቲካ ተሳትፎን የሚጠይቅ ወቅት ላይ እንገኛለን:: ቤተ ክርስቲያን እጅግ ሊቅ የሆኑ ልጆች አሏት፤ እነዚህ ራሳቸውን ሳይደብቁ በዐደባባይ በመውጣት በፖለቲካ

ተወክለው የቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን መብትና ጥቅም ሊያስከብሩ ይገባል። ዕውቀታቸውን ለሕዝባቸው ሰላምና ልማት ሊያውሉት ያስፈልጋል። የሀርን ልማት፣ አንድነትና ሰላም የሚያስጠብቅ የፖለቲካ ርዕዮተን ዓለም ይዘው በመቅረብ ተመራጭ የፖለቲካ ሰዎች እንዲሆኑ ጠንክረው መሥራትም ይጠበቅባቸዋል።

አንዳንድ የዓለማችን ሀገራት ‹‹ክርስቲያናዊ የፖለቲካ ድርጅት›› መሥርተው የሚንቀሳቀሱ እንዳሉ ሁሉ የእኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም የሀገሪቱን ሕግ መሠረት አድርገው ኦርቶዶክሳዊ የፖለቲካ ድርጅት መሥርተው እስከ መንቀሳቀስ ደረጃ መድረስ አለባቸው። በአንዳንድ የዓለማችን ሀገራት ማለትም በኖሮዊ፣ ጀርመን እንዲሁም በሌሎች አንዳንድ የአውሮፓ ሀገራት ካህናት አባቶች በምርጫ ተወዳድረው አሸንፈው የሀገር መሪ እስከመሆን ደርሰዋል። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ካህናት በፖለቲካ ጉዳዮች እንዲሳተፉ ባይፈቀድም ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ልጆች ግን ተሳታፊ መሆን አለባቸው። ካህናት አባቶች ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ትኩረት እንዲሰጡ ከማድረግ ውጪ ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ እንዲሳተፉ አትፈቅድም። የቤተ ክርስቲያን አስታራቂነት ድርሻ እንደተጠበቀ ሆኖ ልጆቿ ፓርላማ ውስጥ ገብተው በሀገሪቱ በሚወሰኑ ማንኛውም ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ማሳለፍ አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን በዚህ ሁኔታ የፖለቲካ ተሳታፊ እንዲሆኑ ታግዛለች። ይህ ካልሆነ ግን በቤተ ክርስቲያንና በሀገር ላይ የሚወሰኑ የፖለቲካ ውሳኔዎችን እንደማንኛውም ገለልተኛ አካል በቴሌቭዥን ከማየት የዘለለ ዕድል አይኖራቸውም።

መንግሥት ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ሃይማኖት የሚወስነው ውሳኔ የሚኖር ከሆነ በፓርላማ ውስጥ ተገኝተው የሚከራከሩና ሐሳብ የሚሰጡ ተወካዮች ከሌሉ ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንቱ ጉዳቷ የበለጠ በዚህ ዘመን ትጎዳለች። በራስ ድክመትና ቸልተኝነት ቤተ ክርስቲያንን መውቀስ ግን ተገቢ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ድረስ መሪዎቿን እየቀባች ስታነግሥ ኖራለች። በኋላ ላይም ርዕዮተ ዓለሙ ተቀይሮ ስትገፋ ቆይታለች።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጫናውን መቋቋም ሲያቅታቸው ክርስትናን ሳይቀር በድብቅ ማስፈጸም መጀመራቸውን እናቀውቃለን። ከዚህ በኋላ የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው የቤተ ክርስቲያን ልጆች ቤተ ክርስቲያን ስትገፋ፣ ክብሯና መብቷ ሲገፋፍ በታዛቢነት ማየት የለባቸውም። ሊሟገቱላት፣ ሊከራከሩላት ክብሯንና መብቷን ሊያስጠብቁላት ይገባል።

ቤተ ክህነቱን ባሉባልታ ከመተቸት ይልቅ የፖለቲካ ተሳታፊ የሆኑ ምእመናን የራሳቸውን ድርሻ መወጣት፤ የቤተ ክህነቱ ጉድለት ደግሞ እንዲስተካከል የተጠናና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ሐሳብ አስተያየት መስጠት አለባቸው። ልጆቻችን ከአባቶች ጋር አላስፈላጊ የሆነ ንትርክ ከማድረግ ወጥተው ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን በጠቅም ከሚችል የፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ መግባት አለባቸው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በዚህ ወቅት በሚኒስቴር ደረጃና በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ እየሠሩ ይገኛሉ። በተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ጭምር በከፍተኛ ኃላፊነት እያገለገሉ ያሉ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ልጆች አሉ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን ከፖለቲካ ውክልና እንዲርቁ አታደርግም።

በተለይ በአገልግሎት ተቋማት በኃላፊነት ላይ ያሉ ልጆቻችን እምነታቸውን በነፃነት የማምለክና የመግለጥ ድክመት አለባቸው። በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ያሉ በእምነታቸው በማፈር በመሸማቀቅ እንዲሁም ኦርቶዶክስ መሆናቸው እንዳይታወቅባቸው ሆነው ሥራን የሚሠሩ እንዳሉ ሁሉ ኦርቶዶክሳዊነታቸውን ሳይደብቁ በኩራት አውጥተው ገልጠው የሚሠሩም በርካቶች ናቸው። ቤተ ክርስቲያንም እንደነዚህ ያሉ ልጆቿን በደንብ ታበረታታለች፤ በቅርበትም ትከታተላለች፣ ትመክራለች፣ ታስተምራለችም። በሌላ የእምነት ተቋማት ሥር ያሉ አንዳንድ የመንግሥት ሠራተኞች በዐደባባይ ሳይፈሩ ሳይሸማቀቁ እምነታቸውን ያስተዋውቃሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ መንግሥትና ሕዝብ የሰጣቸውን አደራ ወደጎን ትተው ለሚከተሉት እምነት ያድራሉ። የእኛ ቤተ ክርስቲያንና ልጆቻችንም ከእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር ትምህርት መውሰድ አለባቸው።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በመጨረሻም ቀረ የሚሉት ነገረ ካለ?

***ብፁዕ ዶ/ር አቡነ አረጋዊ፡-*** ሀገራዊ ምርጫ ሲባል ሀገርን የሚወክልና የሀገርን ዕጣ ፈንታ የሚወስን በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይህንን ከግምት ውስጥ አስገብተው የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ፣ ጥቅምና ክብር የሚያስጠብቅ የፖለቲካ ድርጅት ለመምረጥ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅመውን የፖለቲካ ድርጅት ከምርጫ በፊት ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሀገራችን መልካም ስሟና አንድነቷ ተጠብቆ እንድትዘልቅ እንፈልጋለን፡፡ ሁሉም ዜጎቿ በእኩልነት የሚኖሩባት ሀገር እንድትሆን እንመኛለን፡፡ ሁሉም ዜጋ በሀገሪቱ ባሉ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ የሚሠራባትና የሃይማኖት ነፃነትን የምታከብር እንድትሆንና መጪው ምርጫ ፍትሓዊና ተአማኒ እንዲሆን መሥራት የሁላችንም ድርሻ ሊሆን ይገባል፡፡

**በመጭው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ተወዳድረው የሚያሸንፉ የፖለቲካ ድርጅቶች የተሳሳቱ ትርክቶችን የሚያርሙና ቢቻል በስሑት ትርክት ምክንያት ላለፉት ፴ ዓመታት ጉዳት የደረሰባትን ቤተ ክርስቲያን የሚክሱና ይቅርታ መጠየቅ የሚችል ቅን ልቡና ያላቸው መሆን አለባቸው። በዚህ ዘመን ያለን ሕዝበ ክርስቲያንም የስሑት ትርክት ማወራረጃ መሆን እንደሌለብን ጠንቅቀን በማወቅ በስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ለመሳተፍ የሚያበቃንን ካርድም በመውሰድ በግብታዊነት ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያናችንና ለምእመናን የሚጠቅመውን የፖለቲካ ድርጅት መምረጥ ይጠበቅብናል።**

ገዥው መንግሥትና ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመልካም ዕይታ እንዲያዩና ለሀገርና ለወገን ያበረከተችውን ድረሻ እንዲረዱ እናሳስባለን፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች ቢሆኑ ቤተ ክርስቲያን ማንንም እንዳልበደለችና እንዳልጨቆነች መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ ከአርባ ዓመታት ወዲህ ሆን ተብሎ የጭቆና ማዕከል ስትደረግ እንደቆየች መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በሀገራችን በኢትዮጵያ ዘመናዊ የትምህርት ሥርዓት ባልነበረበት ወቅት ፊደል አስቆጥራለች፤ ታሪክ አቆይታለች፤ ሥነ ጥበብን፣ መድኃኒት ቅመማን፣ የዘመን አቆጣጠርን አስተምራለች፡፡ በሀገራችን አራቱም አቅጣጫዎች ውስጥ የቤተ ክርስቲያን አሻራዎች አሉ፤ እነዚያ ሁሉ የሀገር ሀብት ናቸው፡፡

በሀገራችን ውስጥ እተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በቤተ ክርስቲያን ላይ ሲካሄዱ የነበሩ የተሳሳቱ ትርክቶችን ባለመቀበል፤ ከቤተ ክርስቲያን ጎን በመቆም ለማረም ጥረት ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የተፈጸሙ ስሕተቶች ድጋሜ እንዳይፈጸሙ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ በምርጫው ወቅት ብጥብጥ እንዳይፈጠር ከዚህም ጋር ተያይዞ በወገኖቻችን ላይ ሃይማኖት ተኮር ጥቃት እንዳይፈጸም የፀጥታ አካላት ቀድመው ሊሠሩ ይገባል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ምርጫን ጨምሮ የፖለቲካ ለውጥ ሲካሄድ ቤተ ክርስቲያንና ኦርቶዶክሳውያን ዒላማ ያደረገ ጥቃት ሊፈጸም እንደሚችል ከዚህ ቀደም ካየናቸው ተግባራት እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ወቅት ጥቃት የሚያደርሱ አካላት በስሑት ትርክት የተሞሉና ‹‹የእኔ›› የሚሉትን ሃይማኖት በኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ላይ ለመጫን የሚያልሙ ኃይላት ናቸው፡፡ ይህ ተግባር እንዳይፈጸም መንግሥት ከወዲሁ የሀገራችንን ችግር ስስ ብልት ለይቶ በማወቅ ቅድመ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምርጫ ቦርድም የሀገራችንን ሰላምና ደኅንነት ለማስጠበቅ ሲባል ማድረግ ያለበትን ሁሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** አባታችን ብፁዕ ዶ/ር አቡነ አረጋዊ ውድ ጊዜዎትን ሠውተው ለቃለ መጠይቃችን ስለሰጡን ስፊ ማብራሪያ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን፡፡

***ብፁዕ ዶ/ር አቡነ አረጋዊ፡-*** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ዐቢይ ጾም (ጾመ ሁዳዴ)

**በእህተ ሚካኤል**

***ልጆች! ባለፈው እትማችን ላይ ስለ ዐቢይ ጾም(ጾመ ሁዳዴ) እንዲሁም በጾመ ሁዳዴ ውስጥ የሚገኙ ሳምንታት የየራሳቸው መጠሪያ እንዳላቸው ነግረናችሁ ነበር አስታወሳችሁ? መልካም። የዐቢይ ጾም ሳምንታት ከተሰጣቸው መጠሪያዎች ውስጥ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን ሳምንት ስያሜ « ዘወረደ» እና « ቅድስት» እንደሚባሉ ነግረናችሁ ነበር። እነሆ በዚህ ዝግጅት ቀጥሎ ስላሉት ሁለት ሳምንታት ስለ «ምኩራብ» እና ስለ «መጻጉዕ» እንነግራችኋለን ተከታተሉን።***

## 3. ምኩራብ

ልጆች! ሦስተኛው የዐቢይ ጾም ሳምንት ምኩራብ በመባል ይጠራል። ይህ ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምኩራብ ገብቶ ያስተማረበት ቀን ነው።

ልጆች! የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ምኩራብን « የአይሁድ የጸሎት ቤት » በማለት ይፈታዋል። በብሉይ ኪዳን ዘመን የአይሁድ አምልኮ በኢየሩሳሌም በነበረው ቤተ መቅደስና በሥርዓቱ የተመሠረተ ነበር። ናቡከደነጾር ግን ቤተ መቅደሱን አፈረሰ ሕዝቡንም ወደ ባቢሎን አፈለሰ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አይሁድ በሚገኙባቸው ስፍራዎች ሁሉ ምኩራብ ሊሠሩ እንደጀመሩ ይገመታል። በእስራኤል ሀገር በየቦታው በኢየሩሳሌም ብዙ ምኩራቦች ነበሩ። ሐዋርያትም አይሁዶች በተሰበሰቡባቸው ቦታዎች ሲዘዋወሩ አስቀድመው ወደ ምኩራቦች ገብተው ወንጌልን ያስተምሩ ነበር ይላል። ማቴ ፬፥፳፫ ፤ ሐ.ሥ ፮፥፱

ልጆች በምኩራብ ውስጥ የሕግ እና የነቢያት መጻህፍት የብራና ጥራዞች በሳጥን ውስጥ ይቀመጣሉ። የእግዚአብሔር ቃል ሲነበብ መጽሐፉን የሚያነበው ሰው በደንብ እንዲሰማና እንዲታይ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ቆሞ ያነብ ነበር። የክብር ወንበሮች ከዚህ ቦታ ፊት ለፊት ነበሩ ማቴ ፳፫፥፮ ። ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው ይቀመጡ ነበር።

ምኩራብ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት በአይሁድ የተሰራ የጸሎት ቤት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ተመላልሶ በሚያስተምርበት ጊዜ በአይሁድ ምኩራብ ገብቶ ያስተምር ነበር።

ልጆች! የአይሁድ ፋሲካ ቀርቦ ስለነበር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገባ። ጌታችን ወደ አይሁድ ምኩራብ የገባው የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ነበር። ነገር ግን በቤተ መቅደሱ ብዙ ነጋዴዎች ነበሩ፤ በሬ፣ ላም፣ ፍየል፣ ርግብ የመሳሰሉትን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይሸጡ ይለውጡ ነበር። ጌታችን በተከበረው የእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ብዙ ጫጫታም የማይገባ ነገርም ሲደረግ ተመለከተ። ጅራፍንም ውስዶ ሻጮቹን እየገረፈ ከቤተ መቅደሱ አስወጣ፤ የሚሸጡትንም ነገር ገለባበጠባቸው « የአባቴን ቤት የንግድ ቦታ አታድርጉት፤ ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል» እያለም የእግዚአብሔርን ቃል አስተማራቸው። ዮሐ ፪፥፩– መጨረሻው።

ልጆች! ባጠቃላይ የዐቢይ ጾም ሦስተኛው ሳምንት «ምኩራብ» ተብሎ የተሰየመው ጌታችን መድኃኒታችን ወደ ምኩራብ ገብቶ ስላስተማረና በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚሸጡትን በጅራፍ ገርፎ ያስወጣበት ቀን በመሆኑ ነው።

# 4. መፃጉዕ

ልጆች! የዐቢይ ጾም አራተኛ ሳምንት ‹‹ መፃጉዕ›› በመባል ይታወቃል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ‹‹መጽሐፈ ሰዋሰው መግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ›› በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ‹‹ መፃጉዕ›› ማለት ‹‹ ጉባጣ›› ማለት ነው ብለው ይፈቱታል። የዐቢይ ጾም አራተኛ ሳምንት በዚህ ስያሜ መጠራቱም ጌታችን መድኃኒታችን ኢሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ታሞ አልጋ ላይ የነበረውን በሽተኛ የፈወሰበት ቀን በመሆኑ ነው።

በኢየሩሳሌም ውስጥ በበጎች በር ተብሎ በሚጠራው ስፍራ  አምስት ያህል መመላለሻ የነበረባትና በዕብራይስጥ ቋንቋ ‹‹ቤተ ሳይዳ›› የምትባል አንዲት የመጠመቂያ ቦታ ነበረች። በዚህች ቦታ ብዙ በሽተኞች እየመጡ እየተጠመቁ ከበሽታቸው ይፈወሱ ነበር። በዚህች ቦታ ላይ ሠላሳ ስምንት ዓመት የተኛ በሽተኛ ነበር።

ልጆች! የእግዚአብሔር መልአክ ወደዚህች የመጠመቂያ ቦታ መጥቶ ውሃውን ያንቀሳቅሰው ነበር። መልአኩ ውሃውን ባንቀሳቀሰው ጊዜ በመጀመሪያ የገባ ታማሚ ተፈውሶ ይወጣ ነበር። ስለዚህ መልአኩ ውሃው እንዳንቀሳቀሰ ቀድሞ ለመግባት እና ለመዳን ሽሚያ ነበረ። በዚህ ቦታ ደግሞ ለሠላሳ ስምንት ዓመት የተኛ ምንም ዓይነት ዘመድ ያልነበረው አንድ ሰው ነበረ። ውሃው በመልአኩ በተንቀሳቀሰ ጊዜ የሚወስደው ሰው ባለመኖሩ ለዚያን ያህል ዓመት በዚያች የመጠመቂያ ቦታ ተኝቶ ነበረ።



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጻጉዕን አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ሲለው

በአንድ የሰንበት ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ወደዚህች የመጠመቂያ ቦታ መጣ መፃዕጉንም በአልጋው ላይ ተጣብቆ ተኝቶ አገኘው ለብዙ ዘመናት መተኛቱን ስላወቀም፦ ‹‹ልትድን ትወዳለህን?›› አለው

መፃዕጉዕ ‹‹ጌታ ሆይ ውሃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያው ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ፤ እኔ ወደ መጠመቂያው ልሄድ ስል ሌላው ቀድሞኝ ይገባና ተፈውሶ ይዳል›› በማለት መለሰለት።

ጌታም ‹‹ተነሳና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ›› አለው ወዲያውም መፃጉዕ ዳነ ይተኛበት የነበረውንም አልጋ ተሸክሞ ሄደ። በሽተኛው የተፈወሰበት ቀኑ ሰንበት ነበርና አይሁድ ወደ በሽተኛው መጥተው ‹‹ በሰንበት አልጋህን መሸከም አትችልም ሰንበት ነውና›› አሉት ። መፃዕጉም ‹‹ ከበሽታዬ ያዳነኝ እሱ ነው አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ያለኝ‹  ብሎ መለሰላቸው። እይሁድም ‹‹የፈወሰህን ሰው አሳየን›› አሉት። ነገር ግን በዚያ ቦታ ብዙ ሰው ይጋፋ ነበርና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለይቶ ሊያሳያቸው አልቻለም። ዮሐ ፭፥፩-፲፭ ።

**ልጆች በምኩራብ ውስጥ የሕግ እና የነቢያት መጻህፍት የብራና ጥራዞች በሳጥን ውስጥ ይቀመጣሉ። የእግዚአብሔር ቃል ሲነበብ መጽሐፉን የሚያነበው ሰው በደንብ እንዲሰማና እንዲታይ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ቆሞ ያነብ ነበር። የክብር ወንበሮች ከዚህ ቦታ ፊት ለፊት ነበሩ ማቴ ፳፫፥፮ ። ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው ይቀመጡ ነበር።**

ልጆች! የዐቢይ ጾም አራተኛ ሳምንት መፃጉዕ የተባለበት ምክንያት ከላይ እንደነገርናችሁ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ሳይዳ ተገኝቶ  መፃጉዕን ያዳነበት ቀን ስለሆነ ነው። በሚቀጥለው ዝግጅታችን ስለቀሩት የዐቢይ ጾም ሳምንታት መጠሪያና ታሪክ እንነግራችኂለን እስከዚያው ደህና ሰንብቱ!

*እግዚአብሔር ቸርነት፤*

*የእመቤታችን ፍቅር አይለያችሁ!*

# የዘረኝነት ኑፋቄ

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአሜሪካና በአውሮፓ አንዳንድ በክርስትና ስም የተደራጁ አካላት ክርስትናውን በቆዳ ቀለም ለይተው የጥቁርና የነጭ ቤተ ክርስቲያን ወደሚል ፀረ ክርስትና አደረጃጀት መፍጠር እንደ ጀመሩ ይነገር ነበር። ለስሙ ምስጋና ይሁንና ‹‹ኢየሱስ›› በሚለው ስም በመጠቀምም ‹‹ጥቁሩ ኢየሱስ፣ ነጩ ኢየሱስ›› ወደሚል የጽርፈት ተግባር ውስጥ ገብተዋል።

እነዚህ ወገኖች ‹አንድ አስተምህሮ አለን› እያሉ በዘረኝነት ምክንያት ግን እምነታቸውን መክፈላቸው ያነጋግር ነበር። በአንድ ቋንቋ መሰብሰብ እየቻሉም በዘረኝነት ምክንያት ግን አንድ ስብስብ መፍጠር አለመቻላቸው ጉድ አስብሏል።

በዚህ ተገርመን ሳናበቃ በአህጉራችንና በሀገራችን ክርስትናን በጎሳና በነገድ የሚያይ ወገን ማቆጥቆጥ ጀመረ። የጥቃቱም ዒላማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሆነች።

ቤተ ክርስቲያን በነበራት ታሪክ ውስጥ ብዙ ውጣ ውረድን አልፋ ለሰይጣን የጥፋት ዘር ሳትንበረከክ እዚህ ደርሳለች። በጎጥ ከፋፍለው ጸጋ፣ ቅባት፣ ተዋሕዶ በሚል የነበረውን መለያየት በሊቃውንቷ ጉባኤዎች መትፍሔ ሰጥታ ቤተሰቧን ሁሉ በአንድ ማኅበር አጽንታ ቆይታለች። ለቤተ ክርስቲያን የማይተኛው ሰይጣን ግን አሁን ደግሞ ‹‹የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የእገሌ ጎሳ እምነት እንጂ የእኛ አይደለም›› በሚል መንጋዋን ከቤቱ ለማስበርገግ ሲሠራ ቆይቷል። ብዙዎችም በዚህ አካሔድ ተሰናክለዋል። ኦርቶዶክሳዊ እምነትን በአስተምህሮው ሳይሆን የእነእገሌ እምነት ነው በሚል የጎሰኝት አመለካከት የተለዩት ብዙ ናቸው።

እነዚህ ወገኖች ዓለምአቀፋዊት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ የአንድ ነገድ ብቻ እንደሆነ፣ ለብዙ ዘመናት የኖረችውን ቤተ ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያን አስተምሮ ‹እገሌ የሚባለው ንጉሥ እምነት› በማለት ሲቀሰቀሱ ይታያል። ቢጠይቋት መልስ የማታጣ ስትሆንባቸው፣ ሊቃውንቷን ሊከፋፍሉ ሲሞክሩ ጉባኤዋን መበተን ሲሳናቸው ይህንን የሰነፍ መንገድ ለመጠቀም ተገደዋል።

የመናፍቃኑን የሰነፍ ቅሰጣ ተመልክተን ሳናበቃ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው ቤተ ክርስቲያን በነገድና በጎሳ እንድትደራጅ፣ ከተቻለም እንድትበጣጠስ የሚደረግ ቅስቀሳ እየታየ ነው። ያለውን ፖለቲካዊ ሥርዓት የሚቀየሙና ለፖለቲካዊ ትርፍ የሚሠሩ ሰዎች ሁሉ አሁንም ከቤተ ክርስቲያን ራስ ላይ መውረድ ያለመቻላቸውም ማሳያ ነው። የፖለቲካ ግብግቡን በሌላ ሜዳ ማድረግ ሲሳናቸው በዘረኝት ኑፋቄያቸው ቤተ ክርስቲያንን ሊያውኳት እየሞከሩ ነው። አንዲትን ቤተ ክርስቲያን በአንድ ሀገር ውስጥ ብዙ ሊያደርጓት ይፈልጋሉ። ይህ የሚያስደስተው ማንን ነው? የሚሠሩትስ ለማን ነው? ለሰይጣን አይደለምን?። ይህ ኑፋቄን ለመቀፍቀፍ የሚመች ብቻ ሳይሆን በራሱ ኑፋቄ አይደለምን?

የዘር ጥራትን፣ ቋንቋን፣ መሠረት ያደረገ ማግለል፣ እንዴት ክርስቲያናዊ መንገድ ሊሆን ይችላል? በአንድ ክርስቶስ ወንድማማች ሆነው የኖሩ፣ በአንድ የቁርባን ማዕድ የሚታደሙ ወንድማማቾች መለያየትና አንዱን ለሌላው እንግዳ ማድረግ በክርስትና እንዴት ተቀባይነት ይኖረዋል? ‹በእኛ ዘር ቄስ ብቻ፣ በእኛ ዘር ዲያቆን ብቻ ይገልገል› የሚል ጉባኤ ቢፈጠርስ ይህ የዘር ቤተ ክርስቲያን ክርስቶሳዊ መልኩን እንዴት ያገኛል?

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዎች አብያተ ክርስቲያናት ሲመሠረቱ በአንድ ከተማ በአንድ አካባቢ የሚቋቋሙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉንም በከተማው ወይም በአካባቢው ያሉ የእምነቱን ተከታዮች ያስተናግዳሉ፣

ያቅፉሉ እንጂ የአንድ በቁጥር የበለጠ ወይም ያነሰ ዘር ቤተ ክርስቲያን ሆነው አልተደራጁም፡፡ ስማቸው በከተማው ወይም በአካባቢው የኤፌሶን፣ የአንጾኪያ፣ የኢየሩሳሌም የትያጥሮን፣ የሰርምኔስ ወዘተ ይባላል እንጂ የአይሁድ፣ የግሪክ፣ የሮማዊ እየተባሉ አልተለያዩም፡፡ እግዚአብሔር በሚሰጠው ጸጋ ሁሉ አንድነታቸውን ይጠብቃሉ እንጂ ሰበብ እየፈለጉ አይበጣጠሱም፡፡

የሮማው ንጉሥ ጭካኔ ሮማዊ ዜግነት ወይም ትውልድ የሌላቸውን ሁሉ እንደ እንግዳ እንዲያዩ አላደረገም፡፡ የግሪክ ሰዎች መመካት ግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑትን ክርስቲያኖችን ተለይታችሁ የራሳችሁ ቤተ ክርስቲያን ፍጠሩ አላስባላቸውም፡፡ የአይሁድ ክርስቲያኖች ንቀት ሌሎች የአሕዛብ ወገን ክርስቲያኖች ለብቻቸው ቤተ ክርስቲያን እንዲያቋቁሙ አላደረጋቸውም፡፡

በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በዋናነት ከአይሁድ ወገን የነበሩ ክርስቲያኖችን አብዝቶ ይቀፍ እንጂ ገና ከምሥረታው ጀምሮ ከልዩ ልዩ ሀገር/ነገድ/ የመጡ ክርስቲያኖችም አብረው ያመልኩ ነበር፡፡ የሮም ቤተ ክርስቲያን በአመዛኙ ከአሕዛብ ወገን የነበሩ ክርስያኖችን ይቀፍ እንጂ በርካታ ከአይሁድ ወገን የነበሩ ክርስቲያኖችም ነበሩበት፡፡ ታዲያ በእኛ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች የዚህች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ወይም ትውልድ ነን ካልን የአሁኑን የጎሳ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ከየት አመጣነው? ይህ የሰይጣን ሐሳብ የዓለማውያን መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለሚጭኑ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ያናጋልና ኑፋቄ ነው፡፡ ሊወገዝ የሚገባው የዘረኝነት ኑፋቄ እንደሆነ ታዝቤያለሁ፡፡

እንዲህ ዓይነት ሰዎች የቅዱሳን ሐዋርያትን ማሳሰቢያ መልእክቶች ደጋግመው ማንበብ አለባቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ፣ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ፡፡››(፩ ቆሮ ፩፥፲) ያለው መልእክቱን ያስተውሉ እላለሁ፡፡

**የዘር ጥራትን፣ ቋንቋን፣ መሠረት ያደረገ ማግለል፣ እንዴት ክርስቲያናዊ መንገድ ሊሆን ይችላል? በአንድ ክርስቶስ ወንድማማች ሆነው የኖሩ፣ በአንድ የቁርባን ማዕድ የሚታደሙ ወንድማማቾች መለያየትና አንዱን ለሌላው እንግዳ ማድረግ በክርስትና እንዴት ተቀባይነት ይኖረዋል? ‹በእኛ ዘር ቄስ ብቻ፣ በእኛ ዘር ዲያቆን ብቻ ይገልገል› የሚል ጉባኤ ቢፈጠርስ ይህ የዘር ቤተ ክርስቲያን ክርስቶሳዊ መልኩን እንዴት ያገኛል?**

# ቂሜን እንዴት ልተው?

*ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ሰነበታችሁ? ስሜ ገብረ ሚካኤል ይባላል የምኖረው እዚሁ አዲስ አበባ ሲሆን በድኅረ ገጽ የሚወጡ የስምዐ ጽድቅ እና ሐመር መጽሔት ሥራዎችን እከታተላለሁ። በተለይ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ « ምሥጢሬን ላካፍላችሁ» በሚለው ዐምድ ሥር የሚወጡ ጽሑፎችን ትኩረት ሰጥቼ እከታተላለሁ፤ ብዙ ቁም ነገሮችንም አግኝቼበታለሁ። የራሴን ጥያቄ ላቀርብ የተነሣሣሁትም መልስ ትሰጡኛላችሁ ብዬ በማመን ነው።*

*ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች! ከልጅነት ጀምሮ አብሮ አደግ የሆነ ጓደኛ አለኝ የአንድ ሰፈር ልጆች ስንሆን ከሠላሳ ዓመታት በላይ አብረን ኖረናል። ጓደኛዬን የራሴን ያህል አምነዋለሁ ቤተኛዬም ነው። በአንድ ወቅት በጣም ስለቸገረው ገንዘብ ከመንግሥት ለመበደር ፈልጎ ቤቴን አስይዤ ዋስ ሆንኩት፤ ነገር ግን ገንዘቡን ከወሰደ በኋላ ዕዳውን ለመንግሥት መመለስ ባለመቻሉ የእርሱን ዕዳ ለመክፈል ቤቴ እስከመሸጥ ደረሰ በዚያም ምክንያት ለከፋ ችግር ተጋለጥኩኝ።*

*ይህ የልጅነት ወዳጄ ቤቴ ከመሸጡ በፊት ገንዘቡን እንዲመልስ ብዙ ጊዜ ጠየኩ አስጠየኩት ፤ነገር ግን «ችግሮኝ ነው» በሚል ምክንያት ዕዳውን ሳይከፍል ቀርቶ ለችግር አጋለጠኝ። በፍርድ ቤት እንዳልከሰው «ክርስቲያን ሆኜ» የሚል ይሉኝታ ያዘኝ እንዳልተወው ከላይ እንደጠቀስኩት የከፋ ችግር ላይ ነኝ። እግዚአብሔርን በመፍራት ክሱን ብተወውም ያደረገውን ክፉ ሥራ ግን መርሳት አልቻልኩም። ከነገ ዛሬ ይመልስልኛል በሚል ተስፋ ምንም እንዳልተፈጠረ ስቁ ባናግረውም ያደረገውን ነገር በጥላቻ ከማሰብ አልቦዘንኩም። ቂም ኃጢአት እንደሆነ ባውቅም መተው ግን አልቻልኩም። ጓደኛዬን ባገኙሁትም ሆነ አጠገቤ በሌለ ሰዓት የሠራው ነገር ወደ ልቤ እየመጣ ተቸግሬአለሁ እና በእርሱ ላይ ያለኝን ቂም እንዴት ልተው? መፍትሄ ጠቁሙኝ።*

ገብረ ሚካኤል ‹‹ቂሜን እንዴት ልተው?›› በማለት ቂመኛ እንድትሆን ያደረገህን ምክንያት ዘርዝረህ መፍትሔ ፍለጋ ጥያቄህን ስላቀረብክልን በቅድሚያ ምስጋና እናቀርብልሃለን።

ሰው በሥጋው ሲታመም መታከም ስላለበት የትኛው ሐኪም ቤት ሄዶ የትኛውን የጤና ባለሙያ እንደሚያገኝና ታክሞም ከሕመሙ እንደሚድን በቅድሚያ እንደሚያስበው ሁሉ አንተም በክርስትና ሕይወትህ ላጋጠመህ ፈተናና የኅሊናህ ዕረፍት ለነሳህ ጉዳይ ከእናንተ መፍትሔ አገኛለሁ ብለህ ሳትደብቅ ጥያቄህን አቅርበህልናል። አበው ‹‹በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አያገኝም›› እንዲሉ ።

አንተው እንደገለጽክልን የምትኖረው በአዲስ አበባ ከተማ ሲሆን ከሠላሳ ዓመታት በላይ አብረህ እንደቤተኛ ሆነህ ከምትኖረው ጓደኛህ የገጠመህ ችግር ነው። ልበ አምላክ የተባለውን ንጉሥ ዳዊት ሲያስረዳ ‹‹ከቸር ሰው ጋር ቸር ሁነህ ትገኛለህ፤ ከቅን ሰው ጋር ቅን ሁነህ ትገኛለህ፤ ከንጹሕ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ፤ ከጠማማ ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ።›› መዝ.፲፯፥፳፭-፳፯ ይላል።

ገብረ ሚካኤል በቅድሚያ ከሌላ ሰው ጋር አብሮ አደጌ ነው ጓደኛዬ ነው ብለህ ሙሉ ልብህን ሰጥተህ አብረህ ከመንገዝህ በፊት ልበ አምላክ ዳዊት እንዳለው በተሰጠህ ዕውቀት ጓደኛህን በቅድሚያ መመርመር ግድ ይላል። ቸር ነው፣ ቅን ነው፣ ንጹሕ ነው፣ ጠማማ ነው ለማለት እንኳን ሠላሳ ዓመታትን ይቅርና ጥቂት ወራትም ዓመታትም በቂ ናቸውና። በመጽሐፍ ‹‹የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል?›› ኤር.፲፯፥፱ እንዲል።

መጽሐፍ ቅዱስ በገንዘብ እና በክህደት ምክንያት በቤተሰባቸው ሳይቀር የተፈተኑ ሰዎች መኖራቸውን ይገልጽልናል። ለምሳሌ የያዕቆብን ልጅ ዮሴፍን ለግብጽ ነጋዴዎች የሸጡት የአባቱ ልጆች ወንድሞቹ ናቸው (ዘፍ ፴፯፥፳፯።) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ እንኳን አብሮ አደግ ጓደኛ ይቅርና ‹‹ለሰውም ቤተሰቦቹ ጠላቶቹ ይሆኑበታል›› (ማቴ.፲፥፴፮) ብሎናል። ይህ የሚያሳየን እንኳን በሥጋ የማትዛመደው በሆነ ጊዜ ላይ ያገኘሽው ጓደኛ ይቅርና ቤተሰብ (የሥጋ ዘመድ) እንኳ ቢሆን ላይታመን ይችላል። በመሆኑም የልብ ጓደኛዬ ነው ብለህ ልብህን የጣልክበት ጓደኛህ እንዲህ ዓይነት ሥራ በመሥራቱ ብዙ ሊደንቅህ አይገባም። አንተ

ግን ‹‹ለሚለምንህ ስጥ ከአንተም ይበደር ዘንድ የሚወደውን አትከልክለው›› (ማቴ.፭፥፵፪) የተባለውን አምላካዊ ቃል በመተግበርህ ዋጋህ ሰማያዊ ተግባርህ ክርስቲያናዊ መሆኑ በቅድሚያ ኅሊናህን ልታሳምነው ይገባል።

በእርግጥ ጓደኛህን ከማመንህና ከመውደድህ የተነሳ በተቸገረ ጊዜ ቤትህን አስይዘህ ዋስ እንደሆንክለትና እርሱም ገንዘቡን መክፈል ባለመቻሉ ቤትህን እስከመሸጥ እና ዕዳውን እስከመክፈል መድረስህን በዚህም ለጓደኛህ ስትል ለክፉ ችግር መጋለጥህን ጠቅሰህልናል። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።›› ሮሜ.፰፡፳፰ እንዲል። ጓደኛህ ባደረገህ ነገር እጅግም ሳታዝን ለበጎ ነው ብለህ መቀበል ይገባሃል። በተጨማሪ ራስህን በእርሱ ቦታ ማስቀመጥም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ማንም ሰው በራሱ ፍጹም አይደለምና።

ገብረ ሚካኤል ይህ ፈተና በጓደኛህ በኩል ላንተ መቅረቡ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን ማወቅ ይገባሃል። ፈተናውንም በጸጋ ትቀበል ዘንድ ጽናቱን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው። እንደ ኢትዮጵያዊያን ባሕል ጓደኛህን በሽማግሌ አስጠይቀው። የሽማግሌዎችን ድምፅ አልሰማም ካለም ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ብቻ አሳውቀህ ከልብህ ተውለት። ይቅርታ ማድረግ ምሬትን፣ መብሰልሰልን ስለዚያ ክፉ ነገር በተደጋጋሚ ማሰብን ያስወግዳል። በእርግጥ ይቅርታ ማድረግ በደልን መርሳት ወይም የተሰራውን ስህተት ትክክል ነው ብሎ መቀበል አይደለም ይልቁንም ‹‹ይቅርታ ማድረግ›› በውስጥህ ያሳደረብህን መጥፎ ስሜት መቆጣጠር መቻልና መተው ነው።

በጥያቄህ ውስጥ እንደገለጽክልን ለመክሰስ አስቤ ‹‹ክርስቲያን ሆኜ›› እንዴት እከስዋለሁ እያልኩ ከኅሊናዬ ጋር እየተሟገትኩ እገኛለሁ ብለሃል። ከላይ እንደገለጽክልን በሽማግሌዎች ጠይቀኸው እንቢ ካለ አንተ ቂም መያዝ አይገባህም። ምክንያቱም አበው ‹‹ቂም ይዞ ጸሎት›› ዋጋ እንደሌለው ይገልጻሉና። አንተም ጸሎትህ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ መሻትህን ይፈድምልህ ዘንድ ለነፍስ አባትህ ጉዳዩን አስረዳና ቀኖና ተቀበል።

ስለ ይቅርታ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅ ምሳሌያችን ነው። የሰው ልጆች ያለባቸው እዳ ራሱን አሳልፎ በመስጠት ከፍሏልና። የአዳምን በደልና ኃጢአት ወደዚህ ምድር መምጣቱ ፣ ሥጋን መዋሃዱ ፣ በምድር ላይ ተመላልሶ ማስተማሩ የሰው ልጆች በአዳም ምክንያት ያጡትን ገነት እንዲወርሱ ነበር። ነገር ግን ጌታችን በምድር በነበረበት ጊዜ ላደገላቸው ልካም ነገር ሁሉ ክፉን መልሰውለታል። ይህም ሳይበቃቸው በመስቀል ተሰቅሎ እንዲሞት አድርገውታል። ነገር ግን ያበላቸው፣ ከበሽታ ያዳናቸው፣ ከሰው እኩል ያደረጋቸው በአደባባይ ወጥተው ‹‹ ይሰቀል! ይሰቀል! ይሰቀል!›› ብለው ሲጮሁበት ‹‹አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ›› ሉቃ ፳፫፥፴፬ በማለት ሲጸልይላቸው እናያለን። ገብረ ሚካኤል አንተ ጌታችን ድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደረሰበት በደል የበለጠ በደል፤ ከደረሰበት መከዳት የበለጠ መከዳት አልደረሰብህምና እርሱን አብነት አድርገህ ልትጽናና ይገባሃል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕዳ ስለተያዘው ባርያ እና ዕዳውን ስለሰረዘለት ጌታው በምሳሌ ባስተማረበት አንቀጹ ‹‹መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቆጣጠራቸው የወደደ ንጉሥን ትመስላለች። ሊቆጣጠራቸውም በጀመረ ጊዜ እልፍ መክሊት የሚከፍለውን አንድ ባለ ዕዳ ወደ እርሱ አመጡ። የሚከፍለውም ባጣ ጊዜ ጌታው እርሱንና ሚስቱን፣ ልጆቹም፣ ያለውም ሁሉ እንዲሸጡና ዕዳውን እንዲከፍል አዘዘ። ወዲያውም ያ አገልጋይ ወድቆ ሰገደለት፦ ‹‹ አቤቱ ታገሠኝ ሁሉን እከፍልሃለሁ እያለ ለመነው። ጌታውም ያን አገልጋይ አዘነለትና ፈታው ዕዳውንም ተወለት። . . . ›› ሉቃ ፲፰፥፳፫– ፴፭ ይለናል። ገብረ ሚካኤል አንተም እንደነገርከን ምንም እንኳ ቢቸግርህ ጓደኛህ ቸግሮት ሊከፍልህ ባለመቻሉ ይሆናል ብለህ ነገሩን በቅንነት በማየት ልትተውለት ብሎም በእርሱ ላይ ያለህን ቂም ከውስጥ አውጥተህ ልትጥል ይገባሃል።

በመጽሐፈ ሲራክ እንደተገለጸው ‹‹እንዳንተ ያለውን ሰውን ይቅር ሳትል ኃጢአትህን ያስተሠርይልህ ዘንድ እንግዲህ እንዴት ትለምነዋለህ›› ሲራ ፳፰ ፥ ፬ ብሏልና። በቅድሚያ አንተ የይቅርታ ሰው ሁነህ መገኘት ይገባሃል። ይህ ያንተ ጓደኛ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አንተን በመካዱ ኃጢአት ሠርቷል። ለእርሱ የሥራውን የሚከፍለው እግዚአብሔር እንጂ አንተ ስላልሆንክ ስለተደረገብህ ነገር

ሁሉ ለእግዚአብሔር ንገርለት (ጸልይለት)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና ለሰዎች ግን ኃጢአተኛውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም፡፡›› (ማቴ.፮፥፲፬-፲፭) ይላል፡፡

‹‹በይቅርታ የሚገኝ ድል በጦርነት አይገኝም›› የሚል የኢትዮጵያውያን ብሂልም አለ፡፡ አንተ የበደለህን በተለይም ‹‹ የልቤ ወዳጅ›› የምትለው ሰው ያደረሰብህን በደል መተው በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፊት የምታገኘው ይቅርታ ሲሆን ሁለተኛው ስለ ጓደኛህ የምታስበው መጥፎ ነገር በአንተ ስነ ልቦና ላይ የሚያስከትለውን ጫና ያስቀርልሃል፡፡ አንተም እንዳልከው ወደዚህ ዝግጅት ክፍል እንኳ ለመጻፍ የተገደድከው የጓደኛህ ድርጊት ሰላም ስለነሳህ ነው፡፡ ባንተ ላይ ያደረገውን ነገር ሙሉ በሙሉ ብትተውለት ደግሞ በራስህ ላይ ድልን ትጎናፀፋለህ፣ ሰላማዊ ትሆናለህ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አካላዊና ህሊናዊ ሰላም ለማግኘት እንዲሁም በጤንነት ለመኖር ጓደኛህን ይቅር ማለት ይገባሃል፡፡

ስለዚህ ገብረ ሚካኤል ጓደኛህን ከልብህ ይቅር ማለት የሚገባው ፩ኛ. አንተም በማወቅም ባለማወቅም የሠራኸውን ኃጢአት ይቅር እንድትባል ነው፡፡ አለበለዚያ ይቅር አይላችሁም ተብሏልና፡፡ ፪ኛው ለበደለህ ሰው ይቅርታ ማድረግ የውስጥህን ሰላም ይመልሳልና ነው፡፡ ይልቁንም እንደ ክርስቲያን ለጓኛህም ስመ ክርስትናውን ወደ ገዳማዊ አባቶች ላክና እንዲጸልዩለት አስደርግ፡፡ ‹‹በሰማያት ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁን መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ›› (ማቴ.፭፥፵፭) ተብሏልና፡፡ ጓደኛዬን ባገኝሁትም ሆነ አጠገቤ በሌለ ሰዓት ያደረገኝ ነገር ወደ ልቤ እየመጣ ተቸግሬአለሁ ስላልክ ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች›› (ያዕ.፭፥፲፮) ተብሏልና ለራስህም ወደ ገዳማውያን አባቶች መብዓ ይዘህ በመሄድ እንዲጸልዩልህ አስደርግ፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ብለው መጸለይ እንደሚገባቸው ቅዱሳን ሐዋርያት ጠይቀውት የጸሎት ሁሉ አባት የሆነውን ጸሎት አስተምሯቸዋል፡፡ ማቴ.፮፥፱-፲፫ በዚህ የጸሎት ክፍል ውስጥ ክርስቲያኖች ዘወትር ልብ ብለው ማስተዋል ከሚገባቸው ሐሳቦች ውስጥ አንዱ ‹‹የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፡፡›› የሚለው ጸሎት ነው፡፡ እኛ የበደሉንን ይቅር ካላልን ይቅር አንባልምና ነው፡፡ ይቅር እንድንባል የይቅርታ ሰዎች የፍቅር ሰዎች ሆነን መገኘት ይገባናል፡፡ ‹‹ሙሉ ደመወዝ እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡›› (፪ኛዮሐ.፩፥፰) ተብለናል፡፡ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በክርስትና ጉዞህ ከእግዚአብሔር ሙሉ ደመወዝ እንድትቀበል አንተን እየፈተነ ባለው ቂም ከልብህ ተነቅሎ እንዲጠፋ ከነፍስ አባትህ ጋር ተነጋግረህ ሱባዔ ይዘህበት ጸልይ፡፡ ቂም ይዘህ የምትጸልይ ከሆነ ግን ጸሎትህ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ ለጥያቄ መልስ አያሰጥህም፡፡

ሐዋርያው ‹‹እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን፡፡ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል"፡ ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው ነፍሰ ገዳይ የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይይኖር ታውቃላችሁ፡፡›› (፩ኛ.ዮሐ.፫፥፲፬-፲፭) ብሏል፡፡ ስለዚህ ገብረ ሚካኤል አሁን ካለህበት የሞት መንገድ ወጥተህ በሕይወት መንገድ ለመጓዝ ጓደኛህን ከልብ ይቅር በለው፡፡ ያኔጊዜም እግዚአብሔር የተወሰድብህን ንብረት እንደ ጻድቁ ኢዮብ እጥፍ አድርጎ ይከፍልሃል፡፡ ይህን ካደረግህ ክርስትናውን በዕውቀት ብቻ ሳይሆን በሕይወት ኖረህበታልና፡፡ ምድራዊውን ሀብት ብቻ ሳይሆን ሰማያዊውን ርስት እግዚአብሔር እንደሚያወርስህ እመን፡፡ ‹‹በመልካምና በበጎ ልብ ቃሉን ሰምተው የሚጠብቁት በመጽናናትም ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው፡፡›› ተብሏልና (ሉቃ.፰፥፲፭፡፡)

ገብረ ሚካኤል ቂም እንድንይዝ የሚያደርገን መንፈስ ከጠላት ከዲያብሎስ የሚመጣ መንፈስ ነው፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን ደግሞ በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ እንጂ በጠላት ክፉ መንፈስ መኖር አይገባውም፡፡ ‹‹የጌታችን ጽዋና የአጋንንት ጽዋ ልትጠጡ አትችሉም፣ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ ልትካፈሉ አትችሉም፡፡›› (፩ኛ ቆሮ.፲፥፳፩) ተብሏልና ቂም ኃጢአት መሆኑን እያወቅህ ቂም መያዝ ከአንተ አይጠበቅም፡፡ ‹‹ራቁቱን እንዳይሄድ አፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ለብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው፡፡›› (ራእ.፲፮፥፲፭) ተብሏልና ልብስ የተባለው ልጅነትህን ከቂም ርቀህ ከበቀል ወጥተህ ክርስቲያናዊ ሥርዓትና ሕግን ጠብቀህ ዋጋ እንድታገኝ አምላከ ቅዱሳን ልዑል እግዚአብሔር ይርዳህ፡፡